# ጥናት አንድ ዘፀአት 1፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ወዳጁን አብርሃምን እግዚአብሄር አምላክ እንደ ባህር አሸዋ የማይቆጠር የብዙ ሕዝብ አባት እንደሚያደርገው የሰጠውን የተስፋ ቃል በግብጽ ሃገር ውስጥ ለመጀመር እንደ እርሾ የተጠቀመባቸው የሰዎች ቁጥር ከቁ5 ላይ መረዳት እንደምንችለው ሰባ ሰዎች ብቻ እንደነበሩ እናያለን። ታዲያ እግዚአብሄር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን ተፈጻሚ ለማድረግ ብዙ የተለያዩ መንገዶችን እንደተጠቀመ መናገር ቢቻልም እንኳን፤ ከዚህ ክፍል በተለይም ከቁ6-7 ካለው እንደምናየው እግዚአብሄር የሴቶቹን ማህጸን በመክፈት በፍጥነት እንዲባዙና ከሚሞቱት ይልቅ የሚወለዱት በብዙ እጥፍ በልጠው እንዲገኙ በማድረግ ነው ሃሳቡን የፈጸመው።
2. በዚህ ቁጥር ላይ ጸሐፊው ይህንን ሲል ዮሴፍ የተባለ ሰው በግብጽ ምድር ላይ ኖሮ እንደነበረ አላወቀም ለማለት ሳይሆን፤ እኔ እንደሚመስለኝ ይህ ንጉስ የማያውቀው ምናልባትም በዮሴፍ የሕልም ትርጉምና በዮሴፍ ጥበብ የተሞላ ምክር የግብጽ ምድር ሁሉ ከረሃብና ከጥፋት እንደዳነች የሚያውቀው ነገር የለም ማለት ነው። ይህ ንጉስ በውስጡ የተፈጠረው ፍርሃት፤ በመጀመሪያ ደረጃ በቁጥራቸው እየበለጧቸው መሄዳቸው፣ ሌላው ደግሞ በብርታትም እየበረቱ ነው፣ በጦርነት ጊዜ ከጠላት ጋር አብረው ሊወጓቸው እንደሚችሉ፣ በመጨረሻም በግርግር ጊዜ ከግብጽ ኮብልለው ሊሄዱ የመቻላቸው ጉዳይ ነበረ።
3. አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሰውም ሆነ በቡድን በፈላጭ ቆራጭነት ሥር የሚተዳደሩ አገሮች የችግሩን መፍትሄ ለመስጠት ራሳቸውን በአንደኛ ደረጃ ስለሚያስቀምጡ ከሰዎች ለችግሩ መፍትሄ የሚሆን ነገር ይመጣል ብለው የማመን ችግር አለባቸው፤ ይህ ሰው ግን በቁ10 "...ዘዴ እንፈልግ።" በማለት የሌሎችን ተሳትፎ መፈለጉ ብልህ ያሰኘዋል። ንጉሱ አርቆ በመመልከት ችግር ሊያመጣ ይችላል ብሎ ላሰበውና ሕዝቡን በመፍትሄው እንዲሳተፉ ላደረገበት ነገር በመፍትሄነት ሥራ ላይ ያዋሉት ነገር፤ አንደኛው እስራኤላውያንን እያስጨነቁ የሚያሰሩ አለቆችን ሾሙባቸው፣ ሌላው ደግሞ እስራኤላውያን ለንጉሱ የንብረት ማከማቻን እንዲገነቡ አደረጓቸው።
4. ግብጻዊያኑና በተለይም ንጉሳቸው የነበረው ፍርሃት የእስራኤል ሕዝብ በቁጥሩ እየበዛ የመሄዱ ጉዳይ ሲሆን፤ አሁንም በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ የምንመለከተው ነገር ቢኖር ማስጨነቃቸው በበዛ ቁጥር እንዴት እንደሆነ ባይገባንም እንኳን የእስራኤላውያኑ ቁጥር ከመቀነስ ይልቅ እየጨመረ እንደሄደና በአገሪቱም ሁሉ ላይ እየተስፋፉ እንደሄዱ ስለምናነብ መፍትሄ አድርገው ያሰቡት ነገር ግቡን እንዳልመታ እንረዳለን።
5. አስቀድሞ በግብጽ ንጉስ ውስጥ ብቻ የነበረው የእስራኤል ሕዝብ በቁጥር የመጨመሩ ፍርሃት ቁ12 ላይ ስንመለከት በሕዝቡም ውስጥ ፍርሃትን በመጨመሩ የተነሳ በመፍትሄነት ያመጡት የጭቆና ስትራቴጂ እንዲያውም እያበዛቸው መሆኑን ስላዩ ሌላ ተጨማሪ ነገር መደረግ እንደሚኖርበት በማሰብ በቁ15-16 ላይ የምናየውን ወንዶችን የመግደልና ሴቶችን ግን የማኖር ውሳኔ ላይ እንደደረሱ ይታያል። ንጉሱ ወንዶቹ ተገድለው ሴቶቹ በህይወት እንዲኖሩ ትዕዛዝ የሰጠበት ምክንያት፤ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርሃቱ ወደፊት አይለውብን ሊወጉን ይችላል የሚል ፍርሃት ስለነበረው ሴቶቹ በዚያ ረገድ ችግር ያመጣሉ ብሎ ባለማሰቡ፤ ሌላው ደግሞ ጠለቅ ብሎ ካሰበው ምናልባት ወደፊት ወንዶቹ ባሪያዎች ሞተው ካለቁበትና ሴቶቹን እንደገና ወንዶችን በመውለድ ባሪያዎችን የሚተካበት መንገድ ሊሆን ይችላል።
6. የእስራኤልን ሕጻናት ወንዶች እንዲገድሉ ከንጉሱ ትዕዛዝን የተቀበሉት አዋላጆች፤ በእስራኤል ሴቶችና በግብጻዊያን ሴቶች መሃል እንዳለ አድርገው ለንጉስ ያቀረቡት ምክንያት የጥንካሬ ልዩነት ስላለ አዋላጅም ሳያስፈልጋቸው በራሳቸው በቶሎ እንደሚገላገሉ አድርገው ነው የነገሩት። እግዚአብሄርን በመፍራትና የፈርዖንን ትዕዛዝ ከመታዘዝ እንቢ ብለው ወንዶቹን ልጆች ከሞት በማትረፋቸው ምክንያት እነዚህ ሴቶች ያገኟቸው ሁለት ነገሮች፡ አንደኛው ቁ20 ላይ የምናነበው "እግዚአብሄር መልካም ሆነላቸው" የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቁ21 ላይ የሚገኘው "ቤተሰብ ሰጣቸው" የሚለው ሃሳብ ነው።
7. ቁ20 ላይ ስንመለከት ሕዝቡ አሁንም በቁጥሩ እየበዛና እያየለ ይሄድ እንደነበረ የሚናገር ሃሳብ ስላለ ንጉሱ የጠነሰሰው መፍትሔ እንዳልሰራለት ይጠቁመናል። ይህ መፍትሔ ይሆናል በማለት የተጠቀመባቸው ነገሮች ሁሉ አለመስራታቸውን ንጉሱ በተገነዘበ ጊዜ የፈጠረው ሌላ መፍትሔ፤ በቁ22 ላይ የምናነበው ሲሆን፤ ይህም ለአዋላጆቹ ሰጥቶ የነበረውን ትዕዛዝ በማስፋት ለሕዝቡ ሁሉ የሰጠ መሆኑን እናነባለን።
8. እነ ጴጥሮስ በሐዋ ሥራ ምዕራፍ 5 ውስጥ ለመታዘዝ እንቢ ያሉት የአገሩን ንጉሥ ማለትም ቄሳርን ሳይሆን የካህናቱን አለቆች እንደነበረ እንመለከታለን፤ እነዚህ ሴቶች ግን ትዕዛዙን የተቀበሉት ከማንኛውም ዓይነት ተራ ሰው ሳይሆን ከአገሪቱ ንጉስ ከራሱ ሲሆን እንቢታቸው ሊያስከትለው የሚችለው ነገር ምን እንደነበረ ጠንቅቀው እንደተረዱት አያጠያይቅም፤ ስለዚህም ነው እነዚህ ሁለት ሴቶች ሐዋርያው ጴጥሮስ በሥራ 5፡29 ላይ የተናገረውን ነገር በተግባር ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚ አድርገውታል ብዬ አምናለሁ።

## ጥናት ሁለት ዘፀአት 2፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ሥፍራ የተወለደውን ወንድ ልጅ አስመልክቶ ማወቅ የምንችላቸው ጥቂት ነገሮች አሉ፤ ከእነዚህም የመጀመሪያው ነገር የልጁ አባትና እናት እስራኤላውያን በተለይም ደግሞ ሁለቱም ከሌዊ ወገን መሆናቸውን እናውቃለን፣ በሁለተኛ ደረጃ የምናውቀው ደግሞ በቁ4 ላይ እንደምንመለከተው ከእርሱ በፊት የተወለደች ታላቅ እህት እንደነበረችውም መገንዘብ እንችላለን ማለት ነው። ዘጸ 6፡20ን ስናነብ ስለዚህ ብላቴና አባትና እናት ስም ሲነግረን እንበረምና ዮካቤድ እንደሚባሉ ያረጋግጥልናል።
2. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በእህትነት የወንድሟን ደህንነት ስትከታተል የምንመለከታት ወጣት፤ በዘጸ 6፡20 ውስጥ ስንመለከታት ስሟ ማርያም እንደነበረ መረዳት እንችላለን። የዚህ ልጅ ቤተሰቦች በተለይም በግልጽ የተጻፈልን እናቱ ለሶስት ወራት በመሸሸግ፣ ቅርጫቱን ውሃ እንዳያስገባ በማድረግ በሚገባ በማዘጋጀት ሰዎች ሊያዩት በሚችሉበት ሥፍራ ላይ ማስቀመጧ፤ እህቱ ደግሞ የሚሆነውን ነገር ለመከታተል ጊዜዋን ሰውታ የልጁን ፍጻሜ እስኪታውቅ መከታተሉ ሃላፊነታቸውን እንደተወጡ ያሳየናል።
3. እነዚህ ቤተሰቦች እንደማንኛውም ወላጅ ልጃቸውን ከመውደዳቸው የተነሳ የወሰዱት እርምጃ እንደሚሆን ሁላችን እንገምታለን፤ ሆኖም የእብራዊያን ጸሐፊ እንደሚጠቁመን ከሆነ የእነዚህ ወላጆች ድርጊት የእምነት ድርጊት እንጂ የፍቅር ብቻ እንዳልነበረ ያስገነዝበናል። እግዚአብሄር ይህንን ብላቴና ለመታደግ ሲል አድርጎታል ብዬ የማምናቸው የሚከተሉት ነገሮች ናቸው። አንደኛው የፈርዖን ልጅ ለመታጠብ ያንን ሥፍራ መምሪጧ፣ ሁለተኛ የንጉሥ ልጅ ቅርጫት አይታ የማታውቅ ይመስል በዚያ ቅርጫት ላይ ትኩረቷን ማድረጓ፣ ሶስተኛው ደግሞ እብራዊ እንደሆነ እያወቀችና አባቷ የሰጠውን ትዕዛዝ እያወቀች “አዘነችለት” የሚለው ርህራሄ ከእግዚአብሄር መሆኑን ያረጋግጥልኛል ማለት ነው።
4. እግዚአብሄር የሙሴን ህይወት ማዳን ብቻ ቢሆን አላማው በቤተ መንግሥት ውስጥ ሊያሳድገው ሲችል፤ እርሱ ግን የገዛ ወገኖቹን ማንነትና የሚያመልኩትን የያህዌን ማንነት ጭምር ጠንቅቆ እንዲማር ስለፈለገ በራሱ ወላጅ እናት ሥር አድጎ እንዲማር እህቱን ማርያምን እንደተጠቀመባት እንመለከታለን። በሐዋ ሥራ ምዕራፍ 7 ውስጥ በተለይም ከቁ23-28 ያሉት ክፍሎች የሚያሳዩን በዚህ ክፍል በቁ11 ላይ ሙሴ ወደ ወገኖቹ የወረደው የአርባ ዓመት ሰው በሆነ ጊዜ እንደነበረ መረዳት እንችላለን።
5. ሙሴ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ወገኑን እስራኤላዊውን እየደበደበ የነበረውን ግብጻዊ ከመግደሉ በፊት ያደረገው አንድ ነገር ቢኖር አካባቢውን መቃኘትና ሰው አለመኖሩን ማረጋገጥ ነበረ፤ ምክንያቱም ሊያደርግ ያለው ነገር ልክ እንዳልሆነ ስለሚያውቅና መከራ እንደሚያመጣበት ስለተረዳ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሰው አየኝ አላየኝ ብለን የምናደርጋቸው ነገሮች የጨለማ ሥራ ስለሆኑና የብርሃን ድርጊቶች ስለማይሆኑ አንገታችንን ቀና አድርገን በድፍረት ልንመላለስ የማያስችሉን እንደሆነ ያስተምረናል።
6. እግዚአብሄር ሕዝቡን ከግብጻውያን ጭቆና በሙሴ አማካኝነት ነጻ የማውጣት እቅድ እንደነበረው ለሙሴ በጊዜው ግልጽ አይሁን እንጂ፤ በግብጽ በነበረ ጊዜ የተገፋውንና የተበደለውን ግብጻዊ ነጻ ለማውጣት ሌላውን መግደሉ፣ በእብራዊያንም መሃል አንዱ ሌላውን ማጥቃቱ ልክ እንዳልነበረ መናገሩና፣ በምድያምም ምድር የሴቶቹን መጠቃት አለመፍቀዱ፤ እግዚአብሄር ሕዝቡን ከጥቃት ሊያድን ላቀደው እቅድ የተመቻቸ ልብ እንደነበረው ነው መረዳት የምንችለው። ሙሴ ከእብራዊያን ቤተሰቦች ይወለድ እንጂ አብዛኛውን እድሜውን ሁሉ የኖረው በግብጻዊያን መሃል በመሆኑ በዚያን ሰዓት ምናልባትም አነጋገሩ፣ አለባበሱና ሌላውም ሁኔታው ሁሉ የግብጽን ነገር ስለሚያንጸባርቅ እንደሚሆን አያጠራጥርም።
7. እግዚአብሄር ከአብርሃም፣ ከይስሃቅና ከያዕቆብ ጋራ ያደረገውን ቃል ኪዳን እንዲያስብ ምክንያት ሆኖታል ብሎ ይህ ክፍል የሚናገረው ነገር፤ ሕዝቡ ከመከራቸው ብዛት የተነሳ ያሰሙት ጩኸትና ሲቃ ወደ እግዚአብሄር ጆሮ በመድረሱ እንደሆነ እናያለን። እኔ ከዚህ የምማረው ነገር ቢኖር በችግር ውስጥ ስንሆንና በችግራችን ውስጥ እግዚአብሄር እጁን እንዲያስገባና እንዲረዳን ስንፈልግ ወደእርሱ መጮህ እንደሚኖርብን፤ እርሱ ደግሞ ጩኸታችንን ሰምቶ ለእስራኤል ልጆች እንደገደደው ለእኛም እንደሚገደውና ሊረዳን ዝግጁ እንደሆነ እማራለሁ።
8. በዚህ ክፍል ውስጥ የምናገኛቸው ባልና ሚስት ወይም ደግሞ የሙሴ አባትና እናት በተለይም የዕብራዊያን መጽሐፍ እንደሚነግረን ከሆነ የወሰዱትን ቆራጥ እርምጃ የወሰዱበት ምክንያት በእምነት በመሆኑ እግዚአብሄር ያሳዩትን እምነታቸውን እንዳከበረላቸው ማየት እንችላለን፤ ለዚህም ነው በመጀመሪያ ደረጃ ልጃቸውን ከሞት አፋፍ መውጣት እንዲችል ያደረገው፤ ከዚያም አልፎ ደግሞ ለራሳቸው ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ለመላው የእስራኤል ሕዝብ ደህንነት የሚመጣበት መንገድ አድርጎ እምነታቸውን ተጠቀመበት።

# ጥናት ሶስት ዘፀአት 3፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በግብጽ ምድር ልዑል ሆኖ በቤተ መንግሥት ውስጥ ብዙ ከሥሩ የሚያዛቸውና የሚያስተዳድራቸው ባሪያዎች የነበሩት ይህ ሙሴ፤ በቁ1 ላይ ስንመለከተው ከዝቅታ ሁሉ ዝቅታ የሆነውን የከብት ጠባቂ ሆኖ፤ እንዲያውም እረኛ ብቻ ሳይሆን የራሱ የሆነ አንድ እንኳን ከብት እንዳልነበረው ስናይ፤ ኢየሱስ በሰማየ ሰማያት የነበረውን ክብር ጥሎ ወደ ምድር በመምጣት የወረደበትን ዝቅታ በሁለቱ መሃል ተመሳሳይነትን ያሳየናል። ይህንን ቁጥቋጦ ከሌሎች ከሚቃጠሉ ቁጥቋጦዎች የተለየ የሚያደርጉት ብዬ የማያቸው ሁለት ነገሮች፤ አንደኛው የእግዚአብሄር መልዓክ በቁጥቋጦው ውስጥ መገኘቱና፣ ሁለተኛው ደግሞ ቁጥቋጦ የሚነድ እሳት ቢታይበትም እንኳን አለመቃጠሉ ነው።
2. ሙሴ ከርቀት ሆኖ በተለያዩ ሁኔታዎች ግንዛቤው ሊከፋፈል በሚችልበት ሁኔታ ሊናገረው ስላልፈለገ፤ እግዚአብሄር የሙሴን ያልተከፋፈለ ግንዛቤ ለማግኘት ከመፈለጉ የተነሳ እርሱ ወዳለበት አቅጣጫ እንዲቀርብ እና ሌሎች ትኩረት ሰጥቶ እንዳይሰማ ሊያደርጉት የሚችሉት በአካባቢው የሚሰሙ ድምጾችም ሃሳቡን እንዳይበታትኑበት አስቦ ይመስለኛል። አዎን እላለሁ። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሄር በሚያሳየን ተዓምር ልባችን ተወስዶ በተዓምራቱ አማካኝነት ሊናገረን ያለውን ነገር ሳንሰማ ተዓምራቱን ብቻ አድንቀን ስንሄድ እንታያለን፤ ነገር ግን የተዓምራት ዋነኛው ዓላማ እኛን ማስደነቅ ብቻ ሳይሆን ከተዓምራቱ በስተኋላ የሚገኘውን የተአምራቱን አምላክ ድምጽ እንድንሰማ ለመርዳት መሆኑን እንዳንረሳ ያስፈልገናል።
3. በቁ4 ላይ ሙሴን ካስደነቀው እየተቃጠለ ነገር ግን የማይቃጠል ቁጥቋጦ በተጨማሪ የገጠመው ተዓምራት፤ እንደምናውቀው ሙሴ መጻተኛና በሰው አገር ያለ ምንም ዓይነት ታዋቂንት የሌለው የበጎች እረኛ ሆኖ ሳለ “ሙሴ ሙሴ” በማለት እግዚአብሄር ስሙን አውቆ መጣራቱ ራሱን የቻለ ተአምራት እንደሆነለት አያጠራጥርም። በዚህ ቦታ ላይ እግዚአብሄር ራሱን ሊያስተዋውቅ የተጠቀመበት መንገድ በቁ6 ላይ እንደምናየው “እኔ የአባቶችህ የአብርሃም፣ የይስሃቅ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ አለው።”
4. እነዚህ የምናያቸው ቃላት በሙሉ እያንዳንዳቸው የሚጠቁሙት ተናጋሪው እግዚአብሄር እንደሆነ ነው። የእስራኤል ሕዝብ በዚህ ነገር ውስጥ ምንም አስተዋጽዖ እንዳለው ወይም ደግሞ እግዚአብሄር ከሕዝቡ የሚጠብቀው ተሳትፎ እንዳለ ምንም የሚናገረው ነገር አንመለከትም፤ ምናልባትም አስተዋጽዖ ነበራቸው ከተባለ ወደ እግዚአብሄር መጮህ ብቻ እንደነበረ ነው የምናየው። እግዚአብሄር እስራኤልን ከባርነት ቀንበር ለማላቀቅ ሥራውን ሁሉ የሰራው እርሱ ራሱ እንደሆነ ሁሉ፤ የእኛንም ደህንነት ስንመለከት ከሞት ወደ ሕይወት ለመሻገራችን እኛ እንድንሰራ የተጠየቅነው ነገር አለመኖሩ ሁኔታዎቹን ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል።
5. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሙሴ እግዚአብሄር ላቀረበለት ወደ ግብጽ ሄዶ ሕዝቡን የማዳን ትዕዛዝ ያቀረባቸውን ሁለቱ ጥያቄዎች ስንመረምር፤ በቁ11 ላይ የምናየው ጥያቄ ያተኮረው በሙሴ በራሱ ማንነት (በመልዕክተኛው ማንነት) ላይ ሲሆን፤ በቁ13 ላይ የምንመለከተው ደግሞ ትኩረት ያደረገው በእግዚአብሄር (በላኪው ማንነት) ላይ እንደነበረ እናያለን። ሙሴ ለህዝቡ ጥያቄ መልስ የሚሆነውን ነገር ይጠይቅ እንጂ ወደዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ያመጣው ነገር እርሱ ራሱም የእግዚአብሄን ስምና ማንነቱን ስላላወቀ በመሆኑ ከጥያቄው ያገኘው መልስ እርሱ ራሱ የሚታዘዝለትንና የሚያገለግለውን አምላክ ማንነት ለማወቅ መልካም ነገር ሆኖለታል።
6. በመጀመሪያ የእስራኤል ሽማግሌዎችን መሰብሰብ፣ እግዚአብሄር እንደተገለጠለት መናገር፣ ሕዝቡን እንደጎበኘና መከራቸውን እንደተመለከተ ማስታወቅ፣ ከግብጽ ምድር እንደሚያወጣቸውና ሌሎች የተለያዩ የአህዛብ መንግሥታት ወደሚኖሩባት ማርና ወተት ወደምታፈሰዋ ምድር እንደሚያስገባቸው መንገር ነው። ሙሴና የእስራኤል አለቆች በአንድነት ወደ ፈርዖን ገብተው እንዲጠይቁት የተነገራቸው ጥያቄ፤ ወደ ምድረበዳ የሶስት ቀን መንገድ እንዲጓዙና ለአምላካቸው ለእግዚአብሄር መስዋዕት እንዲያቀርቡ እንዲፈቅድላቸው ነበረ።
7. እግዚአብሄር አምላክ ሙሴና እነዚህ የእስራኤል ሽማግሌዎች ሊጋፈጡት ስላለው ሰው እንደሚያውቅ የተናገረው አንድ ነገር በቁ19 ላይ የምናነበው የፈርዖንን የልብ ጥንካሬና በፈቃደኛነት ታዞ የሚለቃቸው ሰው እንዳልሆነ አስቀድሞ ያውቃል። እግዚአብሄር በታላቅ ክንዱ ነጻ ማውጣቱ ብቻ ሳይሆን በግብጻዊያንም ዘንድ ሞገስ እንደሚሰጣቸውና በዝብዘዋቸው መውጣት እንደሚችሉ አስቀድሞ በመናገር ሲወጡ ባዶ እጃቸውን እንዳይወጡና በዝብዘው እንዲሄዱም ተናግሯቸዋል። ቁ21-22ትን በጥንቃቄ በተግባር ላይ ያላዋለ ቤተሰብ ከግብጻዊያን መውሰድ የሚገባውን ምርኮ ሁሉ ሳያገኝ ባዶ እጁን መቅረት ይችላል።
8. እነዚህ ሁለቱ ማለትም ሙሴ የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዲያወጣቸው በተሰጠው ተልዕኮና፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ ደቀመዛሙርቱ የሰውን ልጆች በሙሉ ከመንፈሳዊ ባርነት ነጻ የሚወጡበትን መንገድ እንዲናገሩ ተልዕኮ በሰጣቸው ወቅት በውስጣቸው ሊሰማቸው የሚችለውን የአለመብቃት ስሜት ለማገዝ የተሰጣቸው ማበረታቻ ለሁለቱም አንድ አይነት ነበረ፤ ይኸውም እኔ ከአንተ ጋራ ነኝ፣ ወይም ደግሞ እኔ ከእናንተ ጋራ ነኝ የሚል ነበረ።

# ጥናት አራት ዘፀአት 4፡1-31(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የመጀመሪያው የሙሴ ጥያቄ የነበረው ነገር "ባያምኑኝስ?" የሚል ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ "ቃሌን ባይቀበሉስ?" የሚለው ሲሆን፤ በሶስተኛነት አስከትሎ የጠየቀው ጥያቄ ደግሞ "እግዚአብሄር አልተገለጠልህም ቢሉኝስ?" የሚለው ነበረ። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር በታናሽ ነገር ታላቅን ተዓምራት ሲሰራ የሚታየው በሙሴ እጅ ውስጥ ምናልባትም ለረጅም ዓመታት በጎችን ሲጠብቅ በነበረበት በእጅ ውስጥ ይዞት ይመላለስ በነበረው በትር ነው።
2. ሙሴ ለእግዚአብሄር የነበሩትን ጥያቄዎች ጠይቆ አስፈላጊውን መልስ ካገኘ በኋላ፤ በዚህ ቁጥር ላይ ተልዕኮውን ለመፈጸም አለመቻሉ ምክንያት አድርጎ ለእግዚአብሄር ሲያቀርብ የምናየው እርሱ አፈ ኮልታፋና መናገር የማይችል ሰው መሆኑን ልክ እግዚአብሄር እንደማያውቅ አድርጎ ሲያስረዳው ነው የምንመለከተው። በቁ11 ከምናነበው ከእግዚአብሄር ምላሽ ውስጥ ለብዙ ሰዎች ዓዕምሮ ጥያቄ ሊፈጥር ይችላል የምለው ሃሳብ፤ ደንቆሮ፣ ዲዳና ዓይነ ሥውር ማድረግ እንዴት ብሎ የእግዚአብሄር ድርጊት ሆኖ ሊቆጠር ይችላል? የሚለው ሃሳብ ነው።
3. እግዚአብሄር ለሙሴ ከሰጣቸው መልሶችና ተአምራቶች ሁሉ በኋላ እንኳን ተስፋ ሳይቆርጥ የመጨረሻ በቁ12 ላይ ሲገባለት የምናየው የተስፋ ቃል፤ እርሱ ራሱ እንዲናገር እንደሚያደርገውና የሚናገረውንም ነገር እንደሚያስተምረው ቃል ሲገባለት ይታያል። ሙሴ ጥያቄውንና ምክንያቱን ባሟጠጠ ጊዜ ለእግዚአብሄር ሲያቀርብለት የምናየው ሃሳብ "ጌታ ሆይ እባክህ ሌላ ሰው ላክ" የሚል ነው። ከሙሴ ለቀረበለት ለዚህ ሃሳብ "የእግዚአብሄር ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ" በማለት ጸሐፊው ይነግረናል።
4. በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ምን ጊዜም ቢሆን እግዚአብሄር ሰዎችን ለምን ይህ ነገር አልገባችሁምና አልተረዳችሁትም፤ ወይም ደግሞ ለምን ጥያቄ ትጠይቁኛላችሁ በማለት ሰዎችን ሲቆጣቸው አንመለከትም፤ ሆኖም ልክ በዚህ ቦታ እንደምናየው የሰዎች አለመታዘዝ ወይም አለማመን ያስቆጣዋል። ከዚህ ለራሳችን መውሰድ የምንችለው ነገር እግዚአብሄር የእምነት እርምጃ እንድንወስድና እንድንታዘዘው በሚጠይቀን ነገሮች ያልገቡን ነገሮች ካሉ መጠየቅ እንጂ እግዚአብሄር አለማመንንና አለመታዘዘን እንደማይወድ መማር እንችላለን።
5. አስቀድሞ እግዚአብሄር ከገባለት ተስፋዎች በተጨማሪ በዚህ ክፍል ሲገባለት የምናያቸው ተስፋዎች፤ የመጀመሪያው አሁን ብቻውን እንደማይሄድና ለፈርዖን በቀጥታ የሚናገረው እርሱ ሳይሆን ወንድሙ አሮን እንደሚሆን ተነገረው፣ ሁለተኛው በትክክል እንዲናገሩ እንደሚረዳቸውና ማድረግ ያለባቸውንም እንደሚያሳያቸው፣ ሌላው ደግሞ የቀድሞው በትሩ ቋሚ ተአምራት መፈጸሚያ እንደምትሆን ተነገረው። ስሟ የተቀየረው የሙሴ በትር ከመባል በቁ20 ላይ "የእግዚአብሄር በትር" ተባለች።
6. ፈርዖን በሙሴ እጅ የተደረጉትን ተዓምራቶች ሁሉ አይቶ ለጊዜው እንደሚለቅ ከተናገረ በኋላ ሁኔታው ሲቀየርለት እንደገና ለመልቀቅ እንቢ ካለ በኋላ እንደሆነ የሚጠቁመን ሃሳብ በቁ23 ላይ የምናነበው የበኩር ልጅን የመግደል ነገር የመጣው ከተዓምራቶቹ ሁሉ መጨረሻና ለመልቀቅ ያስገደደው ተአምር እንደሆነ እናውቃለን። ከሚስቱ ከሲፓራ ድርጊት ከምመለከተው ምናልባትም ወንድ ልጁን ባለመግረዙ ምክንያት ይመስለኛል።
7. ሙሴ እግዚአብሄር ከተናገረው ነገር ተነስቶ አሮንን ሲያገኘው እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ ወደ ግብጽ እንዲሄድ እንደተናገረው መናገር ሲቻል፤ እግዚአብሄር ግን ያደረገው ለአሮንም ሆነ ለሙሴ በመሃል ሊመጣ የሚችለውን ግራ መጋባት ለማስወገድ ለሙሴ የተናገረውን ነገር ለአሮንም ለራሱ መናገሩን ስመለከት፤ ዛሬም እግዚአብሄር እንዲህና እንዲያ እንድታደርግ ነግሮኛል ብለው ለሌላው ሰው ሲናገሩ፤ እግዚአብሄር ለሙሴና ለአሮን በተናገረበት መንገድ ለሌላውም መናገር እንደሚችል ማመን ይኖርብናል።
8. በሙሴ ሕይወት የሚታየው ነገር በተለይም ከህዝቡ እንደጠየቀ እርግጠኛ የሆነባቸውን ጥሩ ጥሩ ጥያቄዎች በመጠየቁ ምክንያት እግዚአብሄር ደግሞ በማያዳግም መንገድ ለእያንዳንዱ መልስ ሰጥቶታል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ከእግዚአብሄር ጋራ በጥያቄና መልስ ጊዜ በማሳለፉ የእግዚአብሄርን ማንነት፣ ስሙን፣ የሃይሉን ታላቅነትና ተአምራቶችንም ሁሉ ፊት ለፊት በማየት ከፊቱ ተደቅኖ ለነበረው ከባድ ተልዕኮ እምነቱን ሊያሳድጉ የሚችሉ ነገሮችን እንዳከማቸ ግልጽ ነው።

# ጥናት አምስት ዘፀአት 5፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ለሙሴና ለአሮን እግዚአብሄር ሕዝቡን ከግብጻውያን ባርነት ለማውጣት ቆርጦ መነሳቱን ለእስራኤላውያን በነገሩበት ወቅት ከጥቂት ተዓምራቶች በኋላ ቃላቸውን እንዳመኑና በእግዚአብሄር እንዳመኑ ስንመለከት፤ ፈርዖንን አስመልክቶ ግን ሙሴ ቀድሞውንም እንደፈራው የእንቢተኛነት መልስ ነው የጠበቃቸው። ፈርዖን ሕዝቡን እንዲለቅ በእግዚአብሄር ለታዘዘው ትዕዛዝ ምላሽ የጠየቀው ጥያቄ "እግዚአብሄር ማንነው?" የሚል ነበረ።
2. በቁ1 ላይ ሕዝቡን ነጻ እንዲለቅ በእግዚአብሄር በተደረገለጥ ጥሪ በመለሰው ምላሽ ላይ የእግዚአብሄርን ማንነት እንደማያውቅ በመናገር ይኽ እግዚአብሄር ማን ነው በማለት ለጠየቀው ጥያቄ በቁ3 ላይ ሙሴና አሮን በድጋሚ እንዲለቅ ማስጠንቀቂያውን ሲያስተላልፉ እግረ መንገዳቸውን እግዚአብሄርን "የእብራዊያን አምላክ" ሲሉ በከፊል መልሱን ይሰጡታል ማለት ነው። ፈርዖን የሙሴንና የአሮንን ድርጊት ሥራ ፈትተው ሥራ የሚያስፈቱ ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ ነው የቆጠራቸው።
3. ፈርዖን በእግዚአብሄር ለተጠየቀው ሕዝቡን ለአምልኮ የመልቀቅ ጥያቄ የእንቢታ መልሱን ከመስጠት ባሻገር፤ በቁ6-9 ላይ እንደምናነበው በሕዝቡ ላይ ሌላ ተጨማሪ ጫና እንዲደረግባቸውና አስቀድሞ ይቀርብላቸው የነበረውን ጭድ ራሳቸው እንዲያቀርቡ እንዲደረግ ሲያዝ ይታያል። ሕዝቡ እግዚአብሄርን ለማምለክ ወደ ምድረበዳ የመሄዳቸውን ጥያቄ ፈርዖን የወሰደበት መንገድ እንደ ስንፍናና ይህንን አይነት ነገር ለማውራት ጊዜ እንደተረፋቸው በማሰብ ነው ተጨማሪ ሥራ የጫነባቸው።
4. እግዚአብሄር ሙሴንና አሮንን የነጻነት መልዕክት በአንደበታቸው በማኖር ወደ ፈርዖን መላኩና እነርሱም ደግሞ ለተሰጣቸው ተልዕኮ ታዛዦች ሆነው ለንጉሱ የተባሉትን በማስተላለፋቸው ምክንያት የእስራኤላውያኑ ሕይወት አበሻ ከድጡ ወደ ማጡ እንደሚለው ሁሉ፤ ቀድሞ ከነበሩበት ወደባሰ ነገር እንደገቡ ቁ10-14 በግልጽ ያሳየናል። የፈርዖንን ከውሃ የቀጠነ ትዕዛዝ ለማሟላት እስራኤላውያኑ አገሩን ሁሉ ይዞሩ እንጂ የተባለውን ያህል ጡብ ማቅረብ እንዳልተቻላቸው በቁ14 ላይ የፈርዖን የባሪያ ተቆጣጣሪዎች ከሚናገሩት ሃሳብ ማረዳት እንችላለን።
5. ምንም እንኳን እስራኤላውያን የእኛ ባሪያዎች ናቸው የፈለግነውንም ልናደርግባቸው እንችላለን የሚለው ሃሳብ በግብጻውያኑ ውስጥ ሰርጾ ያለ ነገር ቢሆንም፤ ይህ አመለካከት የእስራኤላውያንንም ልብና አዕምሮ የያዘ ነገር መሆኑን በቁ15-17 ውስጥ ራሳቸው ከሚናገሩት ንግግር የሚታይ እውነት ነው። የእስራኤላውያን ሃላፊዎች ፈርዖንን በማስተዛዘን ይማጸኑት እንጂ ከእርሱ ያገኙት ምላሽ በምንም ዓይነት መንገድ ከገቡበት ነገር መውጣት እንደማይችሉ ነው የተነገራቸው።
6. ሙሴ በቀጥተኛ አነጋገር እግዚአብሄር እነዚህን ጥፋቶች አጥፍቷል ብሎ የዘረዘረ አይሁን እንጂ፤ ከአነጋገሩ እንደምንረዳው ከሆነ በአንደኛ ደረጃ፤ በዚህ ህዝብ ላይ መከራን ያመጣው እግዚአብሄር እንደሆነ፣ በመቀጠል ደግሞ እኔንም የላከኝ በሕዝቡ ላይ መከራ ለማምጣት ይመስላል፣ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ሕዝቡ ከቀድሞ በባሰ ሁኔታ አበሳውን ሲያይና መከራው ሲደራረብበት አንተ ግን ዝም ብለሃል፣ አልታደግኸውም በማለት በግልጽ ይነግረዋል። እግዚአብሄር ሙሴን ስለጥያቄው አልተቆጣውም፣ ስላለፈው ነገርም አልተናገረውም፤ እግዚአብሄር ያተኮረበት ነገር ቢኖር ሊሰራ ባለውና ቀድሞውንም ለሙሴና ለአሮን በነገረው እውነት ላይ ብቻ ነው።
7. እግዚአብሄር አምላክ አስቀድም ይህ ሁሉ ነገር ከመምጣቱ በፊት ለሙሴ ሊመጣ ያለው ነገር ምን እንደሆነ ግልጽ አድርጎ እንደነገረው በዘጸ 3፡19-20 ከተናገረው ንግግር የምንረዳ ሲሆን፤ ሙሴ ምናልባትም ለጊዜው እግዚአብሄር ሕዝቡን ከባርነት ነጻ ለማድረግ በሚፈጠረው ሁኔታ በህዝቡ ላይ ያለውን ጭነት ማቃለል ባይቻል እንኳን ሁኔታውን ሊያባብስ የሚችል ነገር ውስጥ ያደርሳቸዋል ብሎ የጠበቀ አይመስለኝም፤ ስለዚህም ከሙሴ ምላሽ እንደምመለከተው እግዚአብሄር የሰጠውን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ወይም በትክክል እንዳልተረዳ ወይም ደግሞ እንደረሳው ነው የሚገባኝ።

<u>ጥናት ስድስት ዘፀአት 6፡1-30 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ሕዝቡን ከባርነት ለማስለቀቅና የፈርዖንን እንቢተኛነት ለማሸነፍ በፈርዖንና በእግዚአብሄር መሃል በሚካሄደው ግብ ግብ ላይ፤ የእግዚአብሄር እጅ ስትከብድበት በመጨረሻው የሚወስደውው እርምጃ፤ አንደኛው እንዲሄዱ እንደሚፈቅድላቸውና እንደሚለቃቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን ከዚያብ ባለፈ በቶሎ እንዲለቁለት ከመፈለጉ የተነሳ ያስወጣቸዋል ወይም ያባርራቸዋል በማለት ነው የሚገልጸው። የተስፋ ተቀባዮቹን እንደሰማ ሆኖ የሚያስቆጥረው ነገር ቢኖር፤ በዘፍ 12፡7 ላይ ለአብርሃም ቃል ሲገባ ያለው ነገር ቢኖር፤ ምድሪቱን ለዘሩ እንደሚሰጥና እነዚህ ደግሞ ዘሮቹ ስለሆኑ እንጂ ለአንተ ለራስህ የሚል አንጋገር ስላልተናገረ ነው።
2. ያለ ምንም የሕዝቡ ተሳትፎ እግዚአብሄር ራሱ ብቻውን እንደሚያደርግላቸው ቃል የገባባቸው ስድስቱ ቃላት ወይም ግሶች፡ አወጣችኋለሁ፣ እቤዥችኋለሁ፣ አደርጋችኋለሁ፣ እሆናችኋለሁ፣ አመጣችኋለሁ፣ እሰጣችኋለሁ የሚሉት ናቸው። እግዚአብሄር አምላክ ከሚያደርግላቸው ከእነዚህ ስድስት ነገሮች የተነሳ ቁ7 እንደሚነግረን ከሆነ፤ ከግብጻዊያን ጭቆናና ቀንበር ነጻ ያወጣቸው እግዚአብሄር እርሱ ራሱ ብቻ እንደሆነ የሚረዱበት ደረጃ ላይ እንደሚመጡ ያረጋግጥላቸዋል።
3. ሙሴ ከእግዚአብሄር ተቀብሎ ወደ ሕዝቡ ያመጣው መልዕክት ማንኛውም ሰው በደስታ ሊቀበለውና የምስጋና ምክንያት ሊሆናቸው ሲገባ የእነርሱን አቀባበል ሁኔታ የሚገልጸው አንድ ቃል ግን “አላደመጡትም” የሚል ነው። በልባቸው ደስታን ሊፈጥር የሚገባውን የእግዚአብሄርን የተስፋ ቃል ለመቀበልና ለመደሰት የከለከላቸው ነገር እግዚአብሄር ነጻ እንደሚያወጣቸው የሰጣቸው ተስፋ በፈርዖን እንቢተኛነት የተከለከለ ከመምሰሉም በላይ መከራቸው ከፊት ይልቅ ስለከበደባቸው አዲስ የተስፋ ቃል ለመቀበል ፍላጎትም ሆነ እምነት እንዳልነበራቸው ነው የምናነበው።
4. እግዚአብሄር በፈርዖን እንቢታና ሕዝቡ ተስፋ በመቁረጥ የተሰጣቸውን መልካም የተስፋ ቃሎች እንኳን ለመቀበል ልባቸውን በመዝጋታቸው ምክንያት የተነሳበትን የመጀመሪያውን ተልዕኮ አልቀየረውም፤ በመጀመሪያም ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ፊት ገብተው እንዲናገሩት የተሰጣቸው መልዕክት፤ ወደ ምድረ በዳ ሄዶ እግዚአብሄርን አምላኩን ያመልክ ዘንድ ሕዝቡን እንዲለቅ ሲሆን፤ አሁንም በድጋሚ የተሰጠው ይኸው ትዕዛዝ እንደሆነ እናያለን።
5. ሙሴ ወደ ፈርዖን ተመልሶ መሄድ እንደሌለበት ለእግዚአብሄር ያቀረባቸው ሁለት ምክንያቶች፡ የመጀመሪያው ከላይ እስራኤላውያን ነጻ እንደሚወጡና ብዙ በረከቶች እንደሚጠብቋቸው የተነገራቸው ሰዎች ካልሰሙኝ፤ በመልቀቅ ጥቅሙ የሚቀርበት ንጉስ እንዴት ሊሰማኝ ይችላል የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ገና ተልዕኮውን ሲቀበል የሰጠው ምክንያት “ተብታባ ሰው ነኝ” የሚል ነው። በቁ13 ላይ እንደምንመለከተው እግዚአብሄር መደረግ ያለበትን በድጋሚ መንገር እንጂ ሙሴ ለሚያቀርባቸው ለማንኛቸውም ምክንያቶች መልስ ሲሰጠው አናይም።
6. ቁ20ን በምናነብበት ጊዜ እነዚህ ሁለት የእግዚአብሄርን የነጻነት መልዕክት ይዘው ወደ ንጉሱ ፈርዖን የተላኩት ወንድማማቾች የአባታቸው ስም እንበረም በመባል ሲታወቅ፤ የእናታቸው ስም ደግሞ ዮካብድ በመባል እንደምትጠራ ማየት እንችላለን። እስራኤልን ከባርነት ነጻ ለማውጣት ከእግዚአብሄር የተላኩት እነዚሁ ሰዎች እንደነበሩ ቁ26 እና ቁ27 ግልጽ ባለ ሁኔታ የሚነግሩን ሲሆን፤ በተለይም ቁ26 “…እነዚሁ ነበሩ” ብሎ ነው የሚያስቀምጥልን።
7. ከዚህ ሁኔታ የምማረው ምንም አይነት ብቃት የሌለን ሰዎች ብንሆን እግዚአብሄር ባለንበት ሁኔታ ሊጠቀምብን ከወደደ ሁኔታችን እስኪቀየር ሳንጠብቅ በፈቃደኛነት መሄድ እንደሚኖርብን ነው።
8. በአጠቃላይ ሕዝቡን ለማስለቀቅ አስር መቅሰፍቶች እንደሚያስፈልጉ፣ የመጨረሻው ማስለቀቂያው መቅሰፍት የበኩር ልጆች መሞት መሆኑን እግዚአብሄር እያወቀ ይህንን መረጃ ለሚልከው ሰው አስቀድሞ አለመንገሩ፤ በዘጸ 5፡22-23 ላይ ሙሴ ለተሰማው ስሜት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው። እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ እግዚአብሄር የሙሴን ስሜት ከመጠበቅ ይልቅ፤ የሙሴን ሕይወት በመስራት ላይ እንዳተኮረ ነው የሚታየኝ፤ ስለዚህም አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ መታዘዙን ሲያረጋግጥ ነው የሚቀጥለውን ትዕዛዙን ለመስጠት የወሰነው።

# ጥናት ሰባት ዘፀአት 7፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በምዕራፍ 6 የመጨረሻው ቁጥር ላይ ሙሴ ስለራሱ ያለው አመለካከት ኮልታፋና ለምንም ነገር የማይበቃ ሰው አድርጎ ራሱን የሚያይ ሲሆን፤ እግዚአብሄር ግን በዘጸ 7፡1 ላይ እርሱን የሚያየው ልክ ለፈርዖን እንደ አምላክ ሆኖ የሚለውን ነገር የሚያስፈጽም አድርጎ፤ በተጨማሪም ደግሞ ለእርሱ ብቻ የተመደበ ነብይ የሚኖረው ሰው አድርጎ ነው የሚያየው። እግዚአብሄር ፈቃዱን ለማስተላለፍ የፈለገበት ተዋረድ በሚከተለው መንገድ ነው፡- ከእግዚአብሄር ወደ ሙሴ፣ ከሙሴ ወደ አሮንና፣ ከአሮን ደግሞ ወደ ግብጽ ንጉስ ወደ ፈርዖን መልዕክቱ ይደርሳል ማለት ነው።
2. በቁ3፣ ዘጸ 7፡3፣ 9፡12፣ 10፡20፣ 10፡27 እና እነዚህን የመሳሰሉት ጥቅሶች ሁሉ እግዚአብሄር ራሱ የፈርዖንን ልብ እንዳደነደነ ነው የሚያስመስሉት፤ ሆኖም ገና እግዚአብሄር ሙሴን ሲልከው በ3፡19 ላይ እግዚአብሄር የፈርዖን ልብ የደነደነ እንደሆነና አስቀድሞ ነግሮታል፤ ይህም ማለት የፈርዖን ልብ አስቀድሞም የደነደነ ሲሆን፤ የሰውን ልብ መቀየር የሚችለው አምላክ ለፈርዖን ያንን ጸጋ ለመልቀቅ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ነው የምረዳው። በቁ4 ላይ ሲጠራቸው የምናያቸው ስሞች፤ አንደኛው ሰራዊቴ የሚል ነው፣ ሁለተኛው ደግሞ ሕዝቤ የሚለው ሲሆን፣ ሶስተኛው እስራኤላውያን የሚለው የተለመደው ስማቸውን ነው የተጠቀመው።
3. በምዕራፍ 6 ውስጥ የተመለከትነው የአባታቸውና የእናታቸው ስም የተመለከትን ሲሆን፤ በዚህ ክፍል የምናገኘው መረጃ ደግሞ አሮን የሙሴ ታላቅ ወንድም መሆኑ፣ በሁለቱ መሃል በእድሜም የሶስት ዓመት ልዩነት እንዳለ፣ አሮን የ83 ዓመት ሰው ሲሆን፣ ሙሴ ደግሞ የ80 ዓመት ሰው መሆናቸውን እንገነዘባለን። ህዝቡን እስራኤላውያንን ከነበሩበት የባርነት ቀንበር ማላቀቅ ዋነኛ ዓላማው እንደነበረ ብናውቅም እንኳን፤ ከእነዚህ ቁጥሮች እንደምንረዳው ግብጻውያን ደግሞ እግዚአብሄር ሃያል አምላክ እንደሆነና ከእነርሱ አማልክት ጋራ የሚያስተያዩት እንዳልሆነ ማስተማር ሁለተኛ ግቡ ነው ማለት ይቻላል።
4. ታላቅ ታናሽን ማዘዝ ሲገባው፤ ታናሽ ታላቅን ማዘዙ በእኔ አመለካከት ወደ እግዚአብሄር አሰራር ስንመጣ አገልግሎትን ወይም ሃላፊነትን ሲሰጥ እድሜን ወይም ሌሎች በሰዎች አመለካከት በሚገኙ መመዘኛዎች እንዳልሆነና የራሱ የሆነ የልብ መመዘኛን እንደሚጠቀም ነው የምማረው። በዘጸ 3፡19 ላይ እግዚአብሄር መልዕክተኞቹ ተስፋ እንዳይቆርጡበት ለሙሴና ለአሮን ሊሆን ያለውን ነገር ያስታወቀበትን የመጀመሪያውን ሃሳብ የሚያሳስብ እንደሆነ ነው የምገምተው።
5. እግዚአብሄር ሕዝቡን ነጻ ለማውጣትና ፈርዖን እንዲለቃቸው ለማድረግ በወሰደው እምጃና ላደረገው ተአምር የፈርዖን ምላሽ የነበረው የራሱ የሆኑትን የግብጽ አስማተኞች በማስመጣት እነርሱም ሙሴና አሮን እንዳደረጉት ዓይነት ተዓምር እንዲያደርጉ በማድረግ ለእንቢተኛነቱ ምክንያትን እንደሰጠው ነው የምናየው። የዚህ ዓይነቱ የፈርዖን ድርጊት ሊያስተምረን የሚችለው ነገር፤ ሰዎች እግዚአብሄር የሚያዘጋጅላቸውን መልካም እድል ለመጠቀም ፈቃደኞች የማይሆኑበትና የሆነ ምክንያትን በማዘጋጀት ወደ እግዚአብሄር መንገድ ከመመለስ በራሳቸው ላይ እንቅፋትን ሊያኖሩ እንደሚችሉ እመለከታለሁ።
6. እግዚአብሄር የተአምራት አምላክ እንደሆነና የፈቀደውን ነገር ለማድረግ የሚችል መሆኑን ብንረዳም እንኳን፤ የምናያቸው ተአምራቶች ሁሉ ከእርሱ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ጠንቋዮችና አስማተኞችም ብዛት ያላቸውን ተአምራቶች ሲያደርጉ ይህ ክፍል ያሳየናል፤ ስለዚህም 1ኛ ዮሐ 4፡1 እንደሚነግረን መናፍስት ከእግዚአብሄር ሆነው እንደሆነ ሰዎች ሁሉ ሊመረምሩ ያስፈልጋል።
7. በዚህ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሄርን እየተገዳደረ ያለውና ሕዝቡን ለመልቀቅ ልቡን አደንድኖ የምናየው ሰው ንጉሱ ፈርዖን እንደሆነ እናውቃለን፤ ሆኖም እየሆነ ባለው መቅሰፍት ግን እየተጎዳ ያለው ፈርዖን ብቻ ሳይሆን የአገሩ ተራ ህዝብ ሁሉ የሚጠጣው ውሃ በማጣት በችግር ሆኖ ውሃ ለማግኘት ሌላ ጉድጓድ ቁፋሮ ውስጥ እንደገባ ነው የምናነበው፤ ስለዚህም የእኔ እንቢተኛነትና እልከኛነቴ ሁልጊዜ የሚጎዳው እኔን ብቻ ነው ብለን ማሰብ ሞኝነት ነው።

# ጥናት ስምንት ዘፀአት 8፡1-32 (ለመሪዎች የተዘጋጀ)

1. በእርግጥም እግዚአብሄር አምላክ ፍጥረታት ሁሉ የሚታዘዙለትና አድርጉ ያላቸውን የሚያደርጉለት አምላክ እንደሆነ ይታወቃል፤ ሆኖም እግዚአብሄር በታሪክ ሁሉ ውስጥ ሥራውን ሲሰራ የራሱ የሆኑና ለእርሱ ለመታዘዝ እሺ የሚሉትን ሰዎች በመጠቀም ሥራውን መሥራት እርሱ የመረጠው መንገድ በመሆኑ ዛሬም የሚሰራው ሰዎችን በመጠቀም ነው። ይህ የጓጉንቸር መቅሰፍት ካለፉት መቅሰፍቶች የሚለየው ነገር ቢኖር፤ የቀድሞዎቹ መቅሰፍቶች ሁሉ ቤተ መንግስት ውስጥ፣ ከዚያም እንኳን አልፈው ወደ ፈርዖን መኝታ ቤት ውስጥ እንኳን ሳይቀርና ወደ ሌሎችም ሰዎች ቤት ሁሉ የገባ ሌላ መቅሰፍት እስካሁን አላየንም።
2. እንደ እኔ አመለካከት እግዚአብሄር ህዝቡን ነጻ ለማውጣት አደረጋቸው ተብለው ሁልጊዜ ከሚጠቀሱት መቅሰፍቶች ወይም ተአምራት ጋራ ያልተቆጠሩት የመጣውን መቅሰፍት መልሶ ማጥፋቱ እንዲያውም የሚበልጥ ሆኖ የሚታየኝ አስማተኞቹ ያንን ያደረጉበት ሁኔታ አለማየቴ አስገራሚ ነው ብዬ አምናለሁ።
3. እነዚህን ቁጥሮች የሚያነብ ማንኛውም ሰው ቢሆን ከሆኑት ሁኔታዎች ሁሉ ለአዕምሮ ጥያቄ ሊፈጥር የሚችልና መረዳት ያስቸግራል ብዬ የማስበው ነገር ቢኖር፤ ፈርዖን መቅሰፍቱ ከእርሱ እንዲርቅ ጸሎት መቼ ቢደረግለት እንደሚፈልግ በተጠየቀ ጊዜ የሰጠው ምላሽ ነው፤ ይኸውም አሁኑኑ ጸልዩልኝ ማለት ሲችል ለምን እስከ ነገ ድረስ መቆጠት እንደመረጠ ነው። ጓጉንቸሮችን ፈርዖን በለመነው መልኩ እንዲወገዱ የሚደረግበትን ምክንያት ሙሴ የገለጸው፤ እንደ እግዚአብሄር ያለ አምላክ በምድር ሁሉ ቢፈለግ ሊኖር እንደማይችል ፈርዖንና ሕዝቡ ሁሉ ያውቁ ዘንድ ነው።
4. ፈርዖን ከእግዚአብሄር የመጡበት ክፉ ሁኔታዎች በሙሴና አሮን ጸሎት ከተለወጡለት በኋላ ተመልሶ ወደነበረበት ሁኔታ የሚመለስ መሆኑንና በእንቢተኛነቱ እንደሚቀጥል ከእርሱ ጋራ ያሳለፉት ጊዜ የሚነግራቸው እንደሆነ ይታወቃል፤ ሆኖም ተመልሶ ወደ ፈርዖን የመሄድና ያለመሄድ ውሳኔ በእነርሱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን እግዚአብሄር በቃችሁ ከአሁን በኋላ ወደ እርሱ አትሄዱም እስካላላቸው ድረስ በራሳቸው የሚወስኑት ነገር ባለመሆኑ ነው።
5. እነዚህ ተናካሽ ትንኞች በመባል የተነገረላቸው ነገሮች ቀድሞ በግብጽ ላይ ከመጡት መቅሰፍቶች ሁሉ የሚለየው፤ አንደኛው የፈርዖን ጠንቋዮች እስካሁን የመጡትን መቅሰፍቶች ሁሉ እነርሱም ማድረግ የቻሉ ሲሆን፤ ይህንን መቅሰፍት ግን መድገም አልቻሉም። ሁለተኛው ደግሞ የሌሎቹን መቅሰፍቶች ከእግዚአብሄር መሆናቸውን ሳይናገሩ፤ ይኸ ግን ከእግዚአብሄር መሆኑን ተናግረዋል። አስቀድሞም የፈርዖን ልብ ደንዳና እንደነበረ ለመናገር አስቸጋሪ አይሆንም፤ ሆኖም በዚህ ክፍል ውስጥ የምናየውን ልብ የማደንደን ሁኔታ ልዩ ያደርገዋል የምለው፤ የራሱ አስማተኞች እንኳን ሁኔታው ከእግዚአብሄር መሆኑን ቢመሰክሩለትም አለመቀበሉ ነው።
6. እግዚአብሄር ተጨማሪ መቅሰፍትን በግብጽ ላይ በማምጣት ሕዝቡን ነጻ ከማውጣት ባሻገር ይህ ክፍል የሚያሳየን፤ በፈርዖን ሕዝቦች ማለትም በግብጻውያንና እግዚአብሄር ሕዝብ መሃል ልዩነትን መኖሩን እንዲያውቅ ነው የፈለገው። ፈርዖን እልህ በተያያዘበት ትግል እየተሸነፈ እንደሆነ የሚጠቁመን በቁ25 ላይ የምናየው ሃሳብ ነው፤ "ሂዱና በዚሁ ምድር ለአምላካችሁ ሠው" በማለት መናገሩ ምንም እንኳን የፈቀደላቸው የጠየቁትን ያህል ባይሆንም ከዚህ ቀደም ያልሄደውን ያህል እርምጃ እንደሄደ ነው ይህ አነጋገሩ የሚያሳየን።
7. አስቀድሞ ፈርዖን የእግዚአብሄር ሕዝቦች በዚያው በግብጽ ምድር መስዋዕት መሰዋት እንደሚችሉ ሲናገር፤ ሙሴ ግን ከእግዚአብሄር ጥያቄ ፍንክች አለማለቱን ሲያይ የወሰደው እርምጃ የሶስት ቀን መንገድ ሳይሆን ትንሽ ወጣ ማለት እንደሚችሉ ሲፈቅድላቸው ነው የምናየው። ሕዝቡ ትንሽ ወጣ ብለው ለአምላካቸው እንዲሰው እንደሚፈቅድላቸው ቃል ከመግባት ሌላ፤ ለእርሱ ደግሞ ጸሎት እንዲደረግለትም ጥያቄ ማቅረቡን እዚሁ ማየት እንችላለን።
8. ፈርዖን የራሱን ጠንቋዮች መቅሰፍቱን ከአገሪቱ ላይ እንዲያጠፉለት ከመጠየቅ ይልቅ ሙሴንና አሮንን መጠየቁ ግልጽ የሚያደርግልን ነገር ቢኖር፤ የእርሱ ጠንቋዮች መቅሰፍትን የማምጣት እንጂ መቅሰፍትን የማስወገድ ችሎታ እንደሌላቸው ያሳየናል።

<u>ጥናት ዘጠኝ ዘፀአት 9፡1-35 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በእኔ አመለካከት እግዚአብሄር አምላክ “ሕዝቤን ልቀቅ” ከማለት ይልቅ “ያመልኩኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ” ማለትን የመረጠው፤ ምናልባት እግዚአብሄር እርሱ አምልኮን የሚፈልግ መሆኑን ለግብጻውያን በመንገሩና ያንንም ተከትሎ ብዙ ተአምራቶችንም በማየት ግብጻውያንም ከአማልክቶቻቸው ወደ እርሱ ዘወር እንዲሉ እድል በመስጠት ሁኔታውን ሲያመቻችላቸው ሊሆን ይችላል እላለሁ።
2. ምንም እንኳን ፈርዖን በራሱና በህዝቡ ከብቶች ላይ የደረሰባቸውን ያየ ቢሆንም ወደ እስራኤላውያን ሰፈር ሰዎች ልኮ ያረጋገጠበት ምክንያት እኔ እንደሚመስለኝ፤ እውነትም እግዚአብሄር የተናገረው ነገር በትክክል መፈጸም አለመፈጸሙን እርግጠኛ ለመሆን ነው። ንጉሱ እግዚአብሄር የተናገረው ነገር አንዲት ነገር እንኳን ሳትጓደል መፈጸሙን በገዛ ሰዎቹ ጭምር አረጋግጦ እንኳን ለመታዘዝ እንቢ ማለቱ የልቡን ጥንካሬ ግልጽ አድርጎ ያሳየናል።
3. ምንም እንኳን ፈርዖን የአገሪቱ ተወካይ ሆኖ የተነጋገረ ቢሆንም እንኳን መቅሰፍቶቹ በምድሪቱ ውስጥ በሚገኙት በፈርዖን፣ በሹማምንቶቹና በህዝቡ ሁሉ ላይ እንደነበረ ቁ13-14 ይነግሩናል። በእኔ አመለካከት የዚህ ዓይነቱ የእግዚአብሄር አሰራር የሚያስተምረን ነገር፤ በተደጋጋሚ በህይወታችን የሰራበት የምናውቀውና የተለማመድነው መንገድ አለ ማለት፤ እግዚአብሄር አዲስና የተለየ መንገድን አይጠቀምም በሚለው አስተሳሰብ ተነድተን በምናውቀው  መንገድ ለመሄድ ሳንፈተን፤ እርሱ ምን እንደሚፈልግ ለማወቅ ምሪትን በየጊዜው መቀበል እንደሚኖርብን ነው።
4. እግዚአብሄር ይህንን ለፈርዖን ሲናገር ለእኔ የሚገባኝ፤ አንተንና ህዝብህን በአጠቃላይ ሁሉን ነገር ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ብዙ የተለያይዩ መቅሰፍቶችን ማምጣት ሳያስፈልገኝ በአንድ መቅሰፍት የፈለገውን ማከናወን ይችል እንደ ነበረ፤ ሆኖም ፈርዖንንና ሕዝቡን ከምድር ከማጥፋት በላይ ሃይሉንና ስሙን በምድር ዙሪያ ማሳወቅ ዓላማው እንደነበረ መግለጹ ነው። ይህ በቁ16 ላይ የምናየው በሰዎች አለመታዘዝ ስሙን ማስተዋወቅ እንደሚችል ሲያሳየን፤ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ታዛዦች በሆኑና ራሳቸውን ለእርሱ ባስገዙ ሙሴንና አሮንን በመሰሉ ሰዎች በመጠቀም የሚያደርገው ነው እላለሁ።
5. ለፈርዖን በተነገረው የመቅሰፍት መልዕክት ውስጥ ለእኔ የሚታየኝና የጸጋ መልዕክት ነው ብዬ የማምነው ነገር በቁ19 ላይ የሰፈረው ፈርዖን ከብቶቹን ከዚህ መቅሰፍት ለማዳን የሚችልበትን የመውጫ መንገድም መናገሩ የጸጋውን ምንነት የሚያሳይ ነው እላለሁ። እግዚአብሄር የተናገረውን የጸጋውን ቃል አምነው በመቀበል ከብቶቻቸውን ወደ ቤት ያስገቡ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተነገረውን እንደቀልድ በመውሰድ ከብቶቻቸውን በሜዳ የተው ሹማምንት እንደነበሩ እናነባለን።
6. ምድሪቱ ከባድ በሆነ በረዶ እንደተመታችና ለመቋቋም የማይቻል መቅሰፍት እንደነበረ ፈርዖን ባየ ጊዜ፣ የራሱንና የህዝቡን ሃጥያተኛነት እንዲሁም የእግዚአብሄርን ደግሞ ትክክለኛነት በማወጅ እስራኤልን እንደሚለቅ ከዚህም በኋላ በግብጽ ሃገር የመኖር ግዴታ እንደሌለባቸው ሲናገር ይሰማል። ሙሴ በቁ30 ላይ “አሁንም ቢሆን እግዚአብሄር አምላክን እንደማትፈሩ አውቃለሁ።” በማለት ሲናገር ፈርዖንና ሹማምንቱ ምን እንደሚያስቡ አንብቦ ሳይሆን ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የተመለከተው ነገር ስለነበረ ካለፈው ልምምድ በመነሳት የደረሰበት ድምዳሜ ይመስለኛል።
7. እግዚአብሄር ሁኔታውን ሲቀይረውና መቅሰፍቱን ሲያቆምላቸው ተመልሰው ልባቸውን እንድሚያደነድኑ በቁ30 ላይ የተነበየውን ትንቢት ተፈጻሚ ሲያደርጉት ነው በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናነበው።
8. በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ነገ አስከፊ መቅሰፍት በግብጽ ምድር ላይ እንደሚያመጣ ብቻ ሳይሆን፤ በግብጻውያን ከብቶችና በእስራኤላውያን ከብቶችም መካከል ልዩነትን እንደሚያደርግ ለፈርዖን ግልጽ አድርጎ ሲነግረው ያሳዩን ሲሆን፤ እነዚሁ ቁጥሮች ራሳቸው ልክ እግዚአብሄር እንደተናገረ በነጋታው የተባለው መቅሰፍት መምጣቱ ብቻ ሳይሆን በእስራኤልና በግብጽ ከብቶችም ላይ ልዩነት እንደመጣ ስለሚነግሩን፤ እነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሄር የተናገረውን ነገር አንድም ነገር ሳይቀር የሚፈጽም አምላክ መሆኑን፤ ወይም ደግሞ የገባውን ቃል የሚፈጽም የቃል ኪዳን አምላክ መሆኑን ያረጋግጡልኛል።

# ጥናት አስር ዘፀአት 12፡1-51 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዛሬ እግዚአብሄር በግብጻዊያን ላይ ሊያደርግ ያለው መቅሰፍት በወደፊት የእስራኤል ሕይወት ውስጥ የሚኖረው ተጽዕኖ፤ በቁ2 ላይ እንደምንመለከተው ይህ ወር የዓመታቸው የመጀመሪያው ወር ሆኖ እንዲቆይትዕዛዝ ተሰጥቷቸዋል። ለመምረጥ ነጻነት የተሰጧቸው ነገሮች፡ ቤተሰቡ ለአንድ ጠቦት አነስተኛ መሆኑና አለመሆኑን መወሰን፣ ምን ያህል ጠቦት እንደሚያስፈልግ መጠኑን መወሰን (ቁ4)፣ ጠቦቱ በግ ይሁን ፍየል መወሰን (5)፤ ለመለወጥ ከማይችሏቸው ነገሮች መሃል፡ ጠቦቱ ምንም ነውር የሌለበትና አንድ አመት የሞላው ተባት መሆን አለበት (5)፣ ወሩ በገባ በአስራ አራተኛው ቀን ምሽት ጀምበር ስትጠልቅ መታረድ አለበት (6)።
2. ጠቦቱን ካረዱት በኋላ በመጀመሪያ ደረጃ ከሁሉ ነገር አስቀድመው በቁ7 ላይ እንዲያደርጉ የታዘዙት ነገር ቢኖር፤ ከታረደው ጠቦት የፈሰሰውን ደም ወስደው ጠቦቱ የተበላበትን ቤት ደጃፍ መቃኑንና ጎበኑን እንዲቀቡት ነው። ሥጋውን ጥሬ ወይም ቅቅል ሳይሆን ጠብሰው መብላት አለባቸው፣ ከሥጋው ተርፎ የሚያድር እንዳይኖርና ከተረፈም በእሳት መቃጠል እንደሚኖርበት፣ ሲበሉም ልብሳቸውን ለብሰው፣ ጫማቸውን አድርገው፣ በትራቸውን ይዘው፣ በጥድፊያ እንዲበሉት ነው የተነገራቸው። የሚሰዋው ጠቦት ነውር የሌለበት እንዲሆን መታዘዙ ለእኛ የተሰዋውን ኢየሱስ ምንም ዓይነት ነውር የሌለበት እንደነበረ ያስታውሰኛል።
3. በምዕራፍ አሥራ ሁለት ውስጥ የምናነበውን ተዓምር ከሌሎቹ ተዓምራቶች የተለየ የሚያደርገው ነገር ቢኖር፤ ቁ1-11 መቅሰፍቱ በግብጽ ላይ ከማምጣቱ በፊት የእስራኤል ህዝብ በቅድሚያ ምን ምን ነገሮችን ማድረግ እንደሚጠበቅበት፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ በቁ12-13 ላይ እርሱ ሊያደርግ ያለውን ነገር በመናገር በሁለቱም በኩል መደረግ ያለባቸው ነገሮች እንደነበሩ እንመለከታለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሰፈሩትን ሃሳቦች በአንድ ዓረፍተ ነገር ለመግለጽ፤ "እግዚአብሄር የሰራውን በሕይወታችን የስራቸውን ሥራዎች እንድናስታውስ ይፈልጋል።"
4. ይህ የሙሴ አነጋገር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተከናወነው ነገር የሚለይበት መንገድ፤ በዘጸዓት ውስጥ የምናነበው እያንዳንዱ ቤተሰብ ጠቦት ማረድ ሲጠበቅበት፣ በአዲስ ኪዳን ግን እንደምናውቀው ለዓለም ህዝብ ሁሉ የታረደው አንዱ የእግዚአብሄር በግ መሆኑ ነው። የእስራኤል ልጆች ቤተሰባቸውን ከሚመጣው መቅሰፍት ለማዳን ማድረግ የሚገባቸው ነገር፤ በዚያን ሌሊት ያረዱትን ጠቦት ደም በጎበናቸውና በመቃናቸው ላይ መቀባት ነበረ።
5. በምዕራፍ አምስት ውስጥ ፈርዖን ህዝቡን እንዲለቅ ሲነገረው እግዚአብሄርን አላውቅም፣ ሕዝቡንም አለቅም ባለበት አንደበቱ፤ በ12፡31-32 ላይ ስንመለከተው ግን ለራሱ እንኳን ጸሎት የለመነበት ደረጃ መድረሱ ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሄር ተሰጠ ማለት ባይቻልም እንኳን መለስ ያለ መሆኑን ይጠቁመናል። ፋሲካ የሚለውን ሃሳብ እግዚአብሄር ትኩረት የሚሰጥበት ምክንያት፤ ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች ሁሉ ሊያደርግ ያለውን የሚጠቁም፣ የልጁንም መስዋዕትነት የሚያሳይ ጥላ በመሆኑ ነው።
6. እስራኤል በግብጽ የቆጠው ለአራት መቶ ሰላሳ ዓመታት ነው። አብርሃም ከእግዚአብሄር የተቀበለው የተስፋ ቃል ይህንን ያህል ዘመን ይወስዳል ብሎ የጠበቀ አይመስለኝም። ይህ የሚያስተምረኝ ጌታ የገባውን ቃል መፈጸሙን በእርግጠኛነት ብናውቅም፤ ትክክለኛ ቀኑን እስካልተናገረ ድረስ ምንም ያህል ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል ነው፤ ለዚህም ምሳሌ የኢየሱስ የመምጣቱ ተስፋ ነው።
7. ቁ47 ላይ "የእስራኤል ህዝብ ሁሉ በዓሉን ማክበር ይኖርበታል።" ቁ49 "ይህም ህግ በዜጋውም ሆነ በመካከላችሁ በሚኖሩት መጻተኞች ላይ እኩል ተፈጻሚነት ይኖረዋል።" የሚሉት ጎልተው ከሚታዩኝ መሃል ሁለቱ ናቸው።
8. እግዚአብሄር ግብጻውያንን በዚህ በመጨረሻው መቅሰፍት ከመታቸው በኋላ በምን ዓይነት ሁኔታ ህዝቡን እንደሚያስወጧቸው ሁኔታው ከመሆኑ አስቀድሞ ያውቅ ስለነበረ፤ ህዝቡ በኋላ እንዳይራወጥና ያለጫማ፣ ያለበትር፣ ያለልብስና ወዘተ ከግብጽ ምድር እንዳይወጣ ስለፈለገ አስቀድመው ሙሉ ዝግጅት እንዲያደርጉ ፈልጎ ያደረገው ነገር እንደሆነ ሁኔታው በቁ33 ላይ ሲፈጸም ማየት እንችላለን።

# ጥናት አስራ አንድ ዘፀአት 13፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የግብጻውያንን የበኩር ልጆች በመምታት ማውጣቱን እንዲያስታውሱበት የሰጣቸው መመሪያ፤ እነርሱ ደግሞ የበኩር ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን ማህጸን ከፋች የሆነ እንሥሳንም ሳይቀር ለእግዚአብሄር እንዲቀድሷቸው ነው ያዘዛቸው። እነዚህንና የመሳሰሉትን ክፍሎች ስናነብ፤ “እርሾ” የሚለው ሃሳብ እግዚአብሄር የማይፈልገው፣ ሃጥያት ከሆነ ነገር ጋራ የሚያገናኘው ሲሆን፤ በተለይም የፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እርሾ በማለት ኢየሱስ በብዛት ተጠቅሞበታል።
2. እስራኤላውያን ሊወርሱት በተሰጣቸው ምድር ላይ በጊዜው ይኖሩ እንደነበሩ የተነገሩን ሕዝቦች ሰም እንደሚከተለው ተዘርዝሯል። ከነዓናውያን፣ ኬጢያውያን፣ አሞራዊያን፣ ኤዊያውያንና፣ ኢያቡሳውያን ናቸው። በቁ5 ላይ “እግዚአብሄር ለእናንተ ለመስጠት ሲል…” በማለት የሚናገረው አነጋገር የቃል ኪዳኑ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች የእነ አብርሃም ዘሮች እንጂ እነ አብርሃም ራሳቸው እንዳልነበሩ ግልጽ አድርጎ ያሳየናል።
3. እስራኤላውያኑ በአሉን ሲያከብሩ እነርሱ ራሳቸው ብቻ እግዚአብሄር ከባርነት ምድር ነጻ ስላወጣቸው የሚያከብሩት በዓል እንደሆነ በመረዳት እንዲያደርጉት ብቻ ሳይሆን፤ በተጨማሪም ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ ለልጆቻቸውም ለምን በዓሉን እንደሚያከብሩ ግልጽ እንዲያደርጉላቸው ያስጠነቅቃቸዋል። በቁ8 ላይ የምናነበው አነጋገር የእግዚአብሄር ድርጊት ከጋራ ያለፈና እያንዳንዱ እስራኤላዊ በግሉ እንደተደረገለት መቁጠር እንደሚገባው እንመለከታለን።
4. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ለህዝቡ እንደሚሰጥ የተነገረው ነገር፤ ለአባቶቻቸው በገባላቸው ተስፋ ቃል መሰረት የከነዓንን ምድር እንደሚሰጣቸው የሚነበብ ሲሆን፤ የእስራኤል ሕዝብ ደግሞ ከእግዚአብሄር የሚሰጠውን ስጦታ ከተቀበለ በኋላ እነርሱ ደግሞ የእናቱን ማሕጸን የሚከፍተውን ወንድ ልጅ ለእግዚአብሄር እንደሚሰጡ ነው። የአሰጣጣቸውን ቅደም ተከተል ስንመለከት፤ እስራኤላውያን አስቀድሞ ከእግዚአብሄር ስለተቀበሉት በረከት ምላሽ ነው በኩር ልጃቸውን እንዲሰጡ የተጠየቁት። እኛ አስቀድሞ ከእግዚአብሄር ደህንነትን ስለተቀበልን የምናገለግለው እንጂ፤ ደህንነትን እንዲሰጠን አስቀድመን ልንሰራለት የምንችለው ነገር እንደሌለ መማር እንችላለን።
5. እግዚአብሄር አጭር በሆነው በፍልስጤማውያን መንገድ ቢመራቸውና ጦርነት ሊገጥሟቸው ቢነሱ ሃሳባቸውን ለውጠው ወደ ግብጽ ለመመለስ ልባቸው ሊከጅል ስለሚችል ነው። እግዚአብሄር ለእስራኤላውያን በየትኛው መንገድ መሄድ እንደሚፈልጉ ምርጫን ቢሰጣቸው ኖሮ፤ እንደማናችንም አጭር መንገድ እንዳለ እያወቅን በረዥሙ መንገድ መሄድ እንደማንፈልግ ሁሉ፤ እነርሱም ቢሆኑ ለመሄድ የሚፈልጉት በአጭሩ መንገድ ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለኝም። ከዚህ ሁኔታ መማር የምችለው ነገር፤ እግዚአብሄር አምላካችን የወደፊቱንና ሊመጡ የሚችሉትን ሁኔታዎች ሁሉ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በህይወታችን አንዳንድ ጊዜ አጭር በሚመስለንና ነገር ግን አደጋ ሊያስከትሉብን ከሚችሉ መንገዶች ለመጠበቅ በማንፈልጋቸውና ለጊዜው በማንረዳቸው መንገዶች ሊመራን እንደሚችል እማራለሁ።
6. በዚህ ሥፍራ እግዚአብሄር ህዝቡን በቀን ጸሃይ እንዳያቃጥላቸው በደመና ዓምድ፣ በሌሊት ደግሞ ብርሃን ሊሆንላቸው በእሳት ዓምድ እንደመራቸው እንመለከታለን። ቁ21 እንደሚነግረን እግዚአብሄር ይህንን ያደረገበት ምክንያት ህዝቡ ጉዟቸውን ሳያቋርጡ በቀንም ሆነ በማታ መጓዝ እንዲችሉ እንደሆነ ነው የሚናገረው።

# ጥናት አስራ ሁለት ዘፀአት 14፡1-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እስራኤላውያኑ መከተል የነበረባቸው አንዱ ትዕዛዝ በባህሩ አጠገብ መስፈር ነበረ። እግዚአብሄር በግብጻውያን ላይ ሊፈስም ያለውን ነገር ለማከናወን የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያዘጋጅ ይታያል። ፈርያን እስራኤላውያን ስለሚገኙበት ሁኔታ እንዴት ማሰብ እንዳለበት አመቻችቷል፣ እስራኤል በምን ጊዜ የት መገኘት እንደሚኖርበት ትዕዛዝ ሰጥቷልዷል፤ ፈርያን እስራኤልን ያሳድዳል፤ በፍጻሜው እግዚአብሄር ክብር እንደሚያገኝ፤ ግብጻውያን ደግሞ እግዚአብሄርን እንደሚያውቁ መመልከት እንችላለን።
2. የፈርያን ልብ መደንደኑና የግብጽ ሰራዊት እስራኤልውያንን ከባርነት መውጣት አስቆጭቷቸው እነርሱን መከተል መጀመራቸውን የእስራኤል ልጆች በተመለከቱበት ወቅት እግዚአብሄር ይህንንና ያንን ያደርግልናል የሚል ምንም ዓይነት እምነት ስላልነበራቸው በፍርሃት እንደተዋጡ ምዕራፉን ስናነብ ማየት የምንችል ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሄር ሥራውን ከጨረሰ በኋላ የእስራኤል ልጆች የተሰማቸውን ስሜት ለመረዳት ምዕራፍ 15ትን ማንበብ ስሜታቸውን ሙሉ ለሙሉ ይገልጸዋል።
3. እስራኤላውያኑ ጠላቶቻቸው እንደመጡባቸው በተመለከቱ ጊዜ ያደረጓቸው ሁለት ነገሮች፡ የመጀመሪያው በታላቅ ፍርሃት ወደ እግዚአብሄር መጮህ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በሙሴ ላይ መጮህና ማጉረምረም ነበረ። እነዚህ ሁለት ነገሮች በባህርያቸው የተለያዩ ነገሮች ናቸው፤ ማለትም ሰው በተጨነቀ ጊዜ ወደ እግዚአብሄር መጮህ መልካምና አስፈላጊ ነገር ሆኖ ሳለ፤ እነዚህ ሰዎች ግን ተመልሰው በሙሴ ላይ የተናገሩትን ነገር ስናይ፤ ቀድሞውንም ወደ እግዚአብሄር የጮሁት ጩኸት የእምነት ጩኸት እንዳልሆነ ግልጽ ያደርግልናል። ያወዳደሯቸው ሁለት ነገሮች በምድረ በዳ ከመሞትና፤ ግብጻውያንን ከማገልገል የሚሉት ናቸው።
4. እግዚአብሄር የመጣባቸውን ታላቅ ሰራዊት ድል እንዲያደርግላቸውና ዛሬ የሚያዩአቸውን ግብጻውያን ለዘለዓለም እንዳያዩአቸው ካስፈለገ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሶስት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው። አንደኛው መሸበር አይኖርባቸውም፣ ሁለተኛው ጸንተው መቆም ይኖርባቸዋል፣ ሶስተኛው ደግሞ መታገስ ይጠበቅባቸዋል። እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ፤ እግዚአብሄ ማናቸውንም ነገሮች ለመስራት ያለሰው ማድረግ ይችላል፤ ሆኖም ሰዎችን በማሳተፍና የስራው ተካፋይ እንዲሆኑና በ1ኛ ቆሮ 3፡9 ላይ "ከእርሱ ጋራ አብረን የምንሰራ ነንና" በማለት እንደሚናገረው የሥራው ተካፋዮች እንድንሆን ስለሚፈልግ ይመስለኛል።
5. ፊት ፊት ይሄድ የነበረው መልዓክ ተመልሶ በኋላቸው በኩል ለመከላከል መሄድ፣ የደመናውም ዓምድ በፊት ለፊታቸው ከመሄድ ይልቅ በኋላቸው በኩል መሆን እንደጀመረ፣ መልዓኩም ሆነ ደመናው በእስራኤልና በግብጻውያን መሃል እንደገቡ፣ ደመናው ለአንደኛው ህዝብ ብርሃንን ሲያመጣ ለሌላኛው ሕዝብ ደግሞ ጨለማን በማምጣት አንዳቸው ሌላቸውን ማየት እንዳይችሉ ይከለክል ነበረ። ከዚህ የምማረው ምን ያህል እግዚአብሄር ሕዝቡን ለመከለል ሁኔታዎችን በእቅድ የሚያደርግ እንደሆነ አያለሁ።
6. ሙሴ በቁ13 እና በቁ14 ላይ በተለይም "ዛሬ የምታዩአቸውን ግብጻውያንን ዳግም አታዩአቸውም።" በማለት የተናገረው ንግግርና፤ በቁ28 ላይ ደግሞ የምናነበው "መላውን የግብጽ ሰራዊት ሁሉ ሸፈነ፤ አንድም እንኳን አልተረፈም።" የሚሉት ሃሳቦች ሙሴ የተናገረው ንገር በትክክል ተፈጻሚ ሆኖ እናየዋለን።
7. እግዚአብሄር በግብጻውያን ላይ ያደረገው ተዓምራትና በእስራኤላውያኑ ልብ የሰራው ሥራ ያመጣው ውጤት ሁለት ዋና ዋና ነገሮች እንደሆኑ አያለሁ እነዚህም፡ አንዱ በእስራኤላውያኑ ልብ ውስጥ እግዚአብሄርን መፍራት መግባቱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በእግዚአብሄርና በእግዚአብሄር መልዕክተኛ ማመንን ማስከተሉ ነው።
8. ግብጻውያኑ ሰረገሎቻቸውን በሚገባ መጠቀም እንደሚችሉ ለማንም አጠያያ ጉዳይ አይደለም፤ ሆኖም በዚህ ሥፍራ እግዚአብሄር አምላክ ለህዝቡ መዋጋት በመጀመሩ እነዚህን በችሎታቸው የታወቁት የግብጽ ወታደሮች ሃይላቸውን ለማኮላሸት የተጠቀመበት መንገድ ሰረገሎቻቸውን በማየላለፍ ህዝቡን መከተል እንዳይችሉ ማገድ፤ ከዚያም አልፎ ወራጁ ውሃ እነርሱ እዚያው ባሉበት በላያቸው ላይ መመለስ ነበረ።

## ጥናት አስራ ሶስት ዘፀአት 15፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የእግዚአብሄር ፍርሃት ማለት ሰዎችን የሚያሸማቅቅና ወደ ጭንቀት ውስጥ የሚከት ነገር ይመስላል፤ ሆኖም ግን በዚህ ክፍል የምንመለከተው የእግዚአብሄር ፍርሃት፤ የእግዚአብሄርን ታላቅነት በማድነቅና በማንነቱ በመገረም የሕዝቡን ልብ ወደ አምልኮ የመመለስ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ነው በ15፡1 ላይ የሚታየው። ዳዊትም በዝማሬው እያለ ያለው ነገር፤ እግዚአብሄርን የሚፈሩ ሰዎች ልባቸውን ለምስጋናና ለውዳሴ ማነሳሳት እንደሚኖርባቸው ነው የሚያበረታታው።
2. ለምስጋና ምክንያት ከሆኗቸው ነገሮች መሃል፤ እግዚአብሄር ከፍ ከፍ ማለቱ፣ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባህር ውስጥ መጣሉ፣ እግዚአብሄር ብርታትና ዝማሬአቸው መሆኑ፣ ድነታቸው መሆኑ፣ አምላካቸው ስለሆነ፣ የአባቶቻቸው አምላክ ስለሆነና፣ እግዚአብሄር ተዋጊ ስለሆነ የሚሉት ይገኙበታል። በግብጻዊያን ላይ እግዚአብሄር ያደረጋቸው ነገሮች ደግሞ፡ የፈርዖንን ሰረገሎችና ሰራዊት በባህር ውስጥ ጣለ፣ ምርጥ የሆኑ የፈርዖን ሹማምንት በቀይ ባህር ውስጥ አሰጠመ፣ ጠላቶቹን እንደ ድንጋይ ወደ ጥልቅ አወረደ።
3. በዚህ ቁጥር ላይ በእግዚአብሄር ህዝብ ላይ የተነሳው ጠላት ፍላጎቱና አነሳሱ፤ እስራኤልን እንደሚያሳድድ፣ እንደሚማርክና በዚያም ምርኮን እንደሚካፈል፣ የነፍሱን ወይም የልቡን ፍላጎት በእነርሱ እንደሚያጠግብ፣ ሰይፉን እንደሚመዝና በእጁም እንደሚያጠፋቸው ነው ሲፎክር የሚታየው። የጠላት ጉራና ዛቻ የማያስደነግጠው ሁሉን ቻይ እግዚአብሄር ደግሞ በቁ10 ላይ ምላሽ እንደሰጠ እናያለን፤ ይኸውም እስትንፋሱን እንዳነፈሰ፣ ጠላቶቹን ባህር እንደከደናቸውና፣ ወሃ ውስጥም እንደ ብረት እንዳሰጠማቸው ይነበባል።
4. ጸሐፊው በዚህ ቁጥር ላይ እግዚአብሄርን ከሌሎች አማልክት ልዩ ከሚያደርጉት መሃል የጠቀሳቸው ሶስቱ ነገሮች፤ የመጀመሪያው እግዚአብሄር በቅድስናው የከበረ መሆኑ፣ ሁለተኛው እግዚአብሄር በክብሩ የሚያስፈራ መሆኑና፣ ሶስተኛው ደግሞ እግዚአብሄር ድንቆችን የሚያደርግ መሆኑ ናቸው።
5. እግዚአብሄር ለህዝቡ ያደረገውን ሲሰሙ፤ አህዛብ ወይም የአካባቢው ህዝብ በሙሉ ሰምተው ይንቀጠቀጣሉ፣ የፍልስጤምን ህዝብ ስቃይ ይይዛቸዋል፣ የኤዶም አለቆች ይርዳሉ፣ የሞአብ አለቆች በእንቅጥቃጤ ይያዛሉ፣ የከነዓን ሕዝብ ይቀልጣሉ። እነዚህን መንግሥታት ሁሉ ያስደነግጣሉ በማለት እንደማጠቃለያ የተናገራቸው ሁለት ነገሮች፤ አንዱ የተቤዠውን ህዝብ በማይለወጠው ፍቅሩ መምራቱና፣ ሌላው ደግሞ ሕዝቡን በብርታቱ ወደ ቅዱስ ማደሪያው መምራቱ ናቸው።
6. እግዚአብሄር ለሕዝቡ ያደረገው ድንቅና ተዓምራት እውነትም እስከ ሩቅ ድረስ ባሉት አህዛብ ጆሮ እንደገባና ይህም ወሬ ለብዙዎች ድንጋጤን ያመጣ ነገር እንደነበረ ከዚህች ሴት ንግግር ግልጽ ሆኖ ተመልክቼዋለሁ። እግዚአብሄርን ሕዝብህን አምጥተህ ትተክላከዋለህ በማለት የተነገሩት፤ "ማደሪያህ እንዲሆን በሰራኸው ሥፍራ"፣ "እጆችህ በሰሩት መቅደስ" እና "በርስትህ ተራራ" በመባል ተጠርተዋል።
7. እነዚህ ሰዎች እግዚአብሄር ቀይ ባህርን በመክፈሉ፣ እነርሱን በደረቅ ምድር በማሻገሩና ጠላቶቻቸውን ደግሞ በባህር ውስጥ ማስጠሙ በዝማሬ ሞልቷቸው በተለይም በቁ11 ላይ ድንቆችን ማድረግ የሚችል እንደ እርሱ ያለ አምላክ እንደሌለ አረጋግጠው ሳለ፤ በዚህ ክፍል ግን ያ ሁሉ ነገር ከአዕምሯቸው ጠፍቶ ማጉረምረም ውስጥ እንደገቡ ነው የምናየው። እስራኤላውያኑ ካለፉበት ህይወት ልንማር እንችላለን ብዬ የማምነው ነገር ቢኖር፤ ማጉረምረም ከእኛ ሩቅ ያለ ነገር አድርገን እንዳናስብ፤ ደግሞም የያዝነውን ድልና አምልኮ ሊያስጥለን የሚሞክር ነገር ሊመጣ እንደሚችል አስበን በተጠንቀቅ ህይወታችንን መኖር እንደሚኖርብን እማራለሁ።
8. በቁ22 ላይ ሕዝቡ የነበሩበት ሁኔታ ምድረበዳና ምንም ዓይነት ውሃ የሚባል ነገር የማይገኝበት ቦታ ሲሆኑ፤ በቁ27 ላይ ደግሞ እነዚሁ ሰዎች ውሃ እጅግ በተትረፈረፈበትና ለምለም በሆነ ሥፍራ ላይ ሰፍረው እንደሚገኙ እንመለከታለን። ሕዝቡ አስቸጋሪ በሆነው በዚያ ምድረበዳ ውስጥ እንዲያልፉ የፈቀደበት ምክንያት፤ እኔ እንደሚመስለኝ ገና ሕዝቡ በእግዚአብሄር ማንነት ላይ መደገፍ ስላልተለማመዱ እምነትን ሊያስተምራቸው ነው ብዬ ነው የማምነው።

<u>ጥናት አስራ አራት ዘፀአት 16፡1-36 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በእግዚአብሄር ባሪያዎች ላይ ያጉረመረሙትን የሰዎች ብዛት ሲገልጽ ጸሐፊው "መላው ማህበር" በማጉረምረሙ ላይ ተሳትፎ እንደነበረው አድርጎ ነው የተናገረው። ፀሐፊው መላው ማህበት አጉረመረመ ስላለ፤ በእኔ አመለካከት ምናልባትም እነዚህ ሁለት ሰዎች በዚህ ማጉረምረም ተሳትፈው ሊሆን እንደሚችል፤ ሆኖም እግዚአብሄር መናን ከሰማይ በመስጠትና የተለያዩ ተአምራቶችን በማድረግ ሕዝቡን ሲመራ በማየታቸው በእርሱ ላይ የነበራቸውን እምነት ማሳደግና በእርሱ መታመን ላይ እንደደረሱ እገምታለሁ። በባርነት የነበሩበትን ግብጽ እንደ ምቹና መልካም ቦታ እንደነበረ አድርገው ነው የሚናገሩት።
2. በቁ3 ላይ ስንመለከት የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ምድር አውጥተው በምድረበዳ የሚያንከራትቱት ሙሴና አሮን እንደሆኑ ሲናገሩ፤ በቁ6 ላይ ግን የነገሩን እውነተኛ ገጽታ፤ ማለትም ከግብጽ ምድር ያወጣቸው እግዚአብሄር እንደሆነ ማየት ሊያሳያቸው መሆኑን እንገነዘባለን። ሙሴና አሮን እግዚአብሄር አድርጉ ያላቸውን ነገር ብቻ እየታዘዙ ያሉ እንጂ ከራሳቸው ምንም ዓይነት ነገር ስላላደረጉ፤ ለሚመጣው ማንኛውም ነገር ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው እግዚአብሄር ስለሆነ፤ ለዚህ ነው እግዚአብሄር ያዘዘውን ነገር ለማድረግ በሚተጉ ሰዎች ላይ የሚነሳ ማናቸውም ተቃውሞ በእግዚአብሄር ላይ እንደሚነሳ እንደሆነ መታወቅ የሚኖርበት።
3. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተደጋጋሚ ሲጠቀስ የምናየው አንድ ቃል "ማጉረምረም" የሚል ነው። በእነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ በተደጋጋሚ ስለ ማጉረምረም በተነገረባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ተያይዞ የተነገረው ቃል "ማጉረምረማችሁን ሰምቷልና" የሚል ነው። የእግዚአብሄር ጸሎትን መስማትና ለልመናዎቻችን ጆሮዎቹ የተከፈቱ እንደሆነ ቢታወቅም እንኳን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለምናሰማቸውም ያማጉረምረም ቃላት ወደ እግዚአብሄር ጆሮዎች እንደሚገቡ ይህ ክፍል ያስተምረናል።
4. በዚህ ሥፍራ የእግዚአብሄር መናውን ወደ እያንዳንዱ ሰው ቤት መናው እንዲገባ ማድረግ ሲችል የእርሱ ድርሻ አድርጎ የወሰደው ግን መናውን ማዝነብ ብቻ እንደነበረ ይታያል። በአንጻሩ ደግሞ እስራኤላውያኑ በየቀኑ ወደ ሜዳ በመውጣት እግዚአብሄር የሰጣቸውን መና መሰብሰብና ወደየቤታቸው ማስገባት የእነርሱ ሃላፊነት አድርጎ እንደሰጣቸው ነው የምናነበው። ከአንድ ቀን ያለፈ ነገር መውሰድ እንደማይኖርባቸውና በእያንዳንዱ ቀን እየወጡ ለዚያ ቀን የሚሆናቸውን መሰብሰብ እንደሚኖርባቸው እንደተናገረ ሁሉ፤ "የእለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" የሚለውም የጌታ ጸሎት ከዚህ ሃሳብ ጋራ ይስማማል እላለሁ።
5. በአንዱ ቀን ሸቶ መትላቱና በሌላኛው ቀን ግን ያለመትላቱ ምክንያት፤ አንደኛው ከሰዎቹ ስግብግብነት የተነሳ የእግዚአብሄርን መመሪያ ችላ በማለት የወሰዱት እርምጃ ስለነበረ የተላና የሸተተ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሄር ራሱ ያዘዘውና የደነገገው ነገር ስለነበረ እንኳን ለአንድ ቀን ማደር ይቅርና ቁ33 እንደሚነግረን ከትውልድ እስከ ትውልድ ቆይቶ እንኳን የመሻገትና የመትላት ነገር እንደማያገኘው መመልከት እንችላለን።
6. ቁ 35 ላይ ማንበብ እንደምንችለው፤ እግዚአብሄር ሕዝቡን መና የመገባቸው ዓመታት ቁጥር አርባ እንደነበረ ይታያል። ለአርባ ዓመታት ያህል በተከታታይ ሕዝቡን መና መግቦ የተስፋይቱ ምድር ሲደርሱ ያቆመበት ምክንያት እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ፤ አሁን ሰርተው መመገብ የሚችሉበት ሥፍራ ላይ በመድረሳቸው እግዚአብሄር ስንፍናቸውን የሚያበረታታ ሳይሆን መናን ከሰማይ የሚያወርደው አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ሰዓት ብቻ ስለሆነ ነው ብዬ አምናለሁ።
7. በእኔ አመለካከት በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ላይ የማየው ትልቁ ችግር የእምነት ጉድለት ነው እላለሁ፤ ምክንያቱም ዛሬን እግዚአብሄር መስጠቱን ቢያምኑም እንኳን ይህ ምግብ ነገ ይኑር አይኑር በእነርሱ አስተሳሰብ ማን ያውቃል፤ እንዴት እርግጠኛ መሆን እንችላለን? በሚለው አስተሳሰብ ስለተያዙ ለተጨማሪ ቀኖች የሚበቃውን ያህል መና በመሰብሰብ ለራሳቸው የሚሆነውን መፍትሄ መፈለግ ነው የተያያዙት።

# ጥናት አስራ አምስት ዘፀአት 17፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በምዕራፍ 16 ላይ የእስራኤል ልጆች ችግር ሆኖ የተገኘው ነገር የምግብ አለመኖርና የረሃብ ነገር እንደነበረ እንረዳለን፤ በአንጻሩ ደግሞ ምዕራፍ 17 ውስጥ ገብተን ስንመለከት የእስራኤላውያን ችግር ረሃብ መሆኑ ቀርቶ የውሃ ማጣት ወይም ጥማት እንደነበር ነው የምንመለከተው። በምዕራፍ 16 ላይ ለረሃባቸው እንደ ምክንያት አድርገው የወሰዷቸው ሙሴንና አሮንን ሲሆን፤ በምዕራፍ 17 ላይ ደግሞ ለጥማታቸው ተጠያቂ ሲያደርጉ የምናየው መሪያቸውን ሙሴን ነው።
2. የተጓዙበት መንገድ ሁሉ የእግዚአብሄር ፈቃድ እንደነበረበት የሚጠቁመን ሃሳብ በቁ1 ላይ የሰፈረው "እግዚአብሄር እንዳዘዘው ከስፍራ ወደ ስፍራ ተጉዞ በራፊዲም ሰፈረ" የሚለው አነጋገር ግልጽ በሆነ መንገድ ይህንን እውነት ያስታውቀናል። እነዚህ የእግዚአብሄር ሕዝቦች እግዚአብሄር በፈቀደው መንገድ እንኳን እየተጓዙ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ማለፋቸው፤ እኛም ብንሆን የጌታን ቃልና ትዕዛዙን ተከትለን መሄዳችን ከችግር ነጻ ሊያደርገን እንደማይችልና፤ ሆኖም ዋነኛውና ጥንቃቄ የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር የመጣብንን ችግር በምን ዓይነት ተቀብለን እንደምናስተናግደው ማወቅ መሆኑን መማር እንችላለን።
3. እስራኤላውያኑ ችግር በገጠማቸው ቁጥር ሳያነሱ አልፈውት የማያውቁት አንዱና የሃሳባቸው ማዕከላዊ ሆኖ የሚታየኝ ነገር፤ ከግብጽ የመውጣታቸውን ነገር በጥያቄ ላይ ማስቀመጥ ነው። ምንም እንኳን ሙሴ በተራቡ ጊዜ መና የሰጣችሁን እግዚአብሄርን እንዴት አታምኑትም በማለት መልስ መስጠት ሲችል፤ ሙሴ ግን ከህዝቡ ለመጣበት ማጉረምረም ቅድሚያ ሰጥቶት የምናየው መፍትሄ ችግሩን በእግዚአብሄር ፊት ማቅረብ እንደሆነ እንመለከታለን።
4. ሙሴ ቀድሞ በበትሩ አማካኝነት የተሰሩትን ተአምራቶች በማሰብ ዛሬም ይህች በትር እስካለች ድረስ እንደቀድሞው ተአምራት ይሆናል በሚለው አስተሳሰብ ውስጥ እንዳይገባ እግዚአብሄር በቁ6 ላይ "…እኔ በአንተ ፊት እቆማለሁ" በማለት የመፍትሄው ባለቤት እርሱ መሆኑን እንዳይረሳ ያስታውሰዋል።
5. እግዚአብሄር ሕዝቡን በዚህም ክፍል ሆነ በየትኛውም ሥፍራ ለምን ተራባችሁ ወይም ለምን ተጠማችሁ በሚል ሲቆጣቸው አናይም፤ ሆኖም እግዚአብሄርን የሚያስቆጣው ነገር እግዚአብሄርን ከመለመንና ከመጠየቅ ይልቅ በእርሱ ላይ ማንጎራጎርና ማጉረምረም፤ ከዚያም አልፎ በእርሱ እውነተኛ አገልጋዮች ላይ መነሳታቸው ያስቆጣዋል።
6. ምንም እንኳን ሙሴ ተግቶ እየጸለየ ቢሆንና ድል ተዋጊው እግዚአብሄር ቢሆንም እንኳን እስራኤል እንዲያሸንፍ እግዚአብሄር ያዘጋጀው መንገድ ኢያሱና ህዝቡ ጠንክረው በመዋጋት መሆኑን ነው የሚጠቁመን። ሙሴ እጁን ወደ እግዚአብሄር ዘርግቶ መቆየቱ ለመላው የእስራኤል ህዝብ ይህም ማለት ምናልባትም ከሁለት ሚሊዮን ለማያንስ ህዝብ የመጥፋት ወይም የመዳን ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ስለተረዳ ይመስለኛል ቢደክምም እንኳን የእጁ መውረድ በምንም መንገድ መሆን የሌለበት ነገር ሆኖ የተገኘው።
7. እግዚአብሄር በዚህ ስፍራ በእርሱና በሙሴ መሃል የተካሄደውን ውይይት ኢያሱ እንዲሰማው የፈለገበት ምክንያት፤ እግዚአብሄር ሙሴ በሚሞትበት ሰዓት እርሱን ተክቶ ሕዝቡን የሚመራውና ወደ ተስፋይቱ ሃገር የሚያስገባቸው እርሱ እንደሆነ አስቀድሞ ስለሚያውቅና የአማሌቃውያንን ስም ከምድር ገጽ ላይ ለመደምሰስ ስለሚፈልግ ይህንን አላማውን ወደፊት በሥራ ላይ የሚያውልለት ሰው ኢያሱ ስለነበረ ነው፡
8. በእኔ አመለካከት ሙሴ ይህንን መሰዊያ "እግዚአብሄር አርማዬ ወይም ሰንደቅ ዓላማዬ" በማለት የሰየመበት ምክንያት፤ ህዝቡ ምንም ዓይነት የጦርነት ልምድ ሳይኖራቸው፣ ከግብጽ ምድር ከወጡ ይህ ገና የመጀመሪያ ጦርነታቸው ሆኖ እያለ ብዙ ልምድ ያላቸውንና በደንብ የታጠቁትን አማሌቃውያን በራሳቸው ጉልበት እንዳላሸነፉ፣ ከዚህም በተጨማሪ የእጆቹ ወደላይ መዘርጋትና አለመዘርጋት ያመጣ የነበረውን ልዩነት ሁሉ ሙሴ በመረዳቱ ለዚህ ድል ሊታይና በሰዎች ሁሉ ፊት ሊውለበለብ የሚገባው አንድ ስም ቢኖር የእግዚአብሄር ስም ብቻ መሆኑን በመረዳቱ ነው ብዬ አምናለሁ።

# ጥናት አስራ ስድስት ዘፀአት 18፡1-27 (ለመሪዎች የተዘጋጀ)

1. የሙሴ አማች የሆነው ዮቶር ተነስቶ ሙሴና ሕዝቡ ወደሰፈሩበት ምድረበዳ ለመሄድ ምክንያት የሆነው ነገር፤ ቁ1 እንደሚነግረን እግዚአብሄር ለሙሴና ለህዝቡ ያደረገላቸውንና፣ ከግብጽ ምድር እንዴት እንዳወጣቸው በመስማቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ለዚህ የምድያም ካህን ለዮቶር ይህንን የመሰለ ደስ የሚያሰኝና የሚያበረታታ መልካም ዜና ይዞለት የመጣው ሰው ማን እንደሆነ ገልጾ የሚናገረው ነገር የለም።
2. ይህ ሰው ወደ ሙሴ ለመሄድ በተነሳበት ወቅት ከራሱ ጋራ እንዲሄዱ የወሰዳቸው ሰዎች ስም ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው፡ የሙሴ ሚስት የሆነችው ሲፓራ፣ የበኩር ልጁ ጌርሳምና፣ ሁለተኛ ልጁ አልአዛር ይገኙበታል። ከእነዚህ ቁጥሮች ሙሴ ስለ አማቱ ስለ ዮቶር ስላለው አመለካከት የሚጠቁመን ነገር ትልቅ አክብሮትና ፍቅር እንደነበረው በተለይም ቁ7 ላይ ከሚናገረው ሃሳብ መረዳት እንችላለን።
3. በቁ1 ላይ ስናነብ ዮቶር የሰማው ነገር እግዚአብሄር ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት እንዴት አድርጎ ነጻ እንዳወጣቸው ሲሆን፤ ከሙሴ ጋራ በተገናኘበት ወቅት የሰማው አዲስ ነገር ብዬ የምለው፤ በመንገዳቸውም ላይ ብዙ ዓይነት ፈተናዎች ገጥመዋቸው እንደነበረና በዚያ ሁሉ ውስጥም እግዚአብሄርም እንዴት እንደረዳቸው መስማቱ ነው። እግዚአብሄር ለህዝቡ የሰራውን ሥራ መስማቱ ዮቶር "እግዚአብሄር ከአማልክት ሁሉ በላይ ሃያል እንደሆነ አሁን አወቅሁ።" ወደሚለው መሰረታዊ እውነት አመለካከቱን መልሶለታል።
4. የሙሴ አሰራር በዮቶር አዕምሮ ውስጥ የፈጠረው ጥያቄ፤ ይህንን የሚያህል ሕዝብ ሁል ቀኑን ሙሉ በጠራራ ፀሐይ ሙሴን ብቻ ቆሞ በመጠበቅ የሚውልበት ምክንያት ለምን እንደሆነ ሊገባውና ሊረዳው ባለመቻሉ ጥያቄ እንደፈጠረበትና ጥያቄውንም ራሱን ሙሴን እንደጠየቀው ነው የምናነበው። አንደኛው የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመፈለግና፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እርስ በእርሳቸው ክርክር ሲኖራቸው ለፍርድ ወደ እርሱ ይመጣሉ።
5. በቁ17 እና በቁ18 ውስጥ በሙሴ የሥራ ክፍፍል በሌለበት ዓይነት አሰራር ምክንያት እየተጎዱ ያሉ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ሲናገር፤ የመጀመሪያው ተጎጂ ሆኖ የቀረበው ሕዝቡን ብቻውን እያገለገለ ድካምና ከባድ ሸክም እንደሆነበት የተነገረው ሲሆን፤ ሁለተኛው ተጎጂ ደግሞ የእግዚአብሄርን ፈቃድና፣ ፍርድን ፈልጎ በመምጣት በጸሐይ የሚቆላው ሕዝብ ነው።
6. ሙሴን በዚህ ሥራ ለመርዳት የሚሾሙት ሰዎች መመዘኛ ሆነው በዚህ ቦታ የተነገሩት ነገሮች፡ እነዚህ ሰዎች ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፣ ሰዎቹ እግዚአብሄርን የሚፈሩ ሊሆኑ ይገባል፣ ታማኞችና በማታለል የሚገኘውን ጥቅም የሚጸየፉ መሆን ይኖርባቸዋል። ሥራውን ለረዳቶቹ ካከፋፈለ በኋላ የሙሴ ሥራ የሚሆነው ቁ19 እና 20 ላይ እንደምናየው እርሱ በእግዚአብሄር ፊት የህዝቡ ተወካይ ይሆናል፣ ክርክራቸውን ወደ እግዚአብሄር ያመጣል፣ የእግዚአብሄርን ሕግና ሥርዓት ያስተምራቸዋል፣ እንዴት መኖር እንዳለባቸውና ምን መስራት እንደሚገባቸው ያሳያቸዋል።
7. ሙሴ አማቱ ዮቶር የመከረውን ምክር ሁሉ በሥራ ላይ ቢያውለው ሊያስገኝ ይችላል ብሎ በቁ23 ላይ የተናገረው ነገር፤ አንደኛ ሙሴ ራሱ ካለበት ድካሙ ማረፍና ድካሙን መቋቋም ይችላል፤ ሁለተኛ ሕዝቡ ደግሞ ረክተው ወደየቤቶቻቸው መሄድ ይችላሉ። ዮቶር ሙሴ ይሄድበት የነበረው መንገድ ትክክል እንዳልነበረና የተሻለውን መፍትሄ በመናገሩ ምክንያት ግንኙነታቸው እንዳልሻከረ የሚጠቁመን ሃሳብ በቁ27 ላይ የምናነበው ነው።
8. በእኔ አመለካከት በመጀመሪያ ደረጃ ዮቶርን ትልቅ ሰው ሊያሰኘው የሚያበቃው ነገር፤ ከሙሴ ጋራ ያለውን ጓደኝነት ወይም ግንኙነት ማቆየትን ቅድሚያ ሳይሰጥ እውነቱን በፍቅር ከመናገር በግልጽ ለሙሴ ጥፋቱን በመንገር የሚስተካከልበትንም የመፍትሄ ሃሳብ መስጠቱ ትልቅ ያሰኘዋል። ሙሴ ደግሞ የዚያ ሁሉ ሕዝብ መሪ ሆኖ ሳለ ይህ ሰው ይህ ሰው የሰጠውን ምክር ተቀብሎ ትዕቢት ሳያሸንፈው በተግባር መተርጎሙ ትልቅ ሰው ያሰኘዋል።

# ጥናት አስራ ሰባት ዘፀአት 19፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ገና ምዕራፉ ሲጀምር በቁ1 ላይ ከምናነበው ሃሳብ እንደምንረዳው ከሆነ ሙሴ ገና ወደ እግዚአብሄር ተራራ ሳይወጣና ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳያደርግ እዚያ ሥፍራ የደረሱበትን ጊዜ ጸሐፊው ሲነግረን ከግብጽ ከወጡ ልክ እቅጯን ሶስት ወር ነው ይለናል፤ ስለዚህም ቢያንስ ቢያንስ ሶስት ወራት ያለ አስርቱ ትዕዛዛት ተጉዘዋል ለማለት ያስችለናል።
2. እስራኤላውያኑ የስሚ ስሚ ወይም ደግሞ በወሬ ያገኙት መረጃ ሳይሆን በገዛ ዓይኖቻቸው እንዳዩት በማረጋገጥ የሚነግራቸው ሁለቱ ነገሮች፤ የመጀመሪያው ባሪያ አድርገው ይገዟቸው በነበሩት ግብጻውያን ላይ ያደረገውን ነገር፣ ሁለተኛው ደግሞ እነርሱን ራሳቸውን በንስር ክንፍ ተሸክሞ ወደ እርሱ ማምጣቱን ነው። እግዚአብሄር በንስር ክንፍ ተሸክምኩ ሲል ብዙ ነገሮችን ሊያጠቃልል የሚችል ሲሆን ከእነዚህ ሁሉ ጥቂቶቹን ለመዘርዘር ቢያስፈልግ፡ ግብጻውያን ሲመጡባቸው በባህር ውስጥ ማስጠሙ፣ እነርሱን ደግሞ በደረቅ ምድር ማሻገሩ፣ ሲርባቸው መና መስጠቱ፣ ሲጠማቸው ውሃ ማፍለቁና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።
3. ከዚህ ሁኔታ ለእኛ ህይወት ትምህርት ሊሆን ይችላል የምለው ነገር ቢኖር፤ እግዚአብሂር አምላክ ለእርሱ እንድንገዛና እንድንታዘዝ የሚፈልግ አምላክ ቢሆንም እንኳን፤ ገና በጠላት እስራት ውስጥ ያለና ለሌላ ጌታ እየተገዛን ባለንበት ወቅት ሳይሆን ዛሬ የእርሱ ልጆችና ሕዝቡ ካደረገን በኋላ ግን የእርሱን ትዕዛዝና ህግ በመጠበቅ እንድንኖር እንደሚጠብቅብን እማራለሁ።
4. ሕዝቡን ከነበሩበት እስራት ነጻ ለማውጣት ግብጻውያንን በተለያየ መቅሰፍት በሚመታበት ጊዜ፣ ወይም ደግሞ በንስር ክንፍ ተሸከምኳችሁ በማለት የተናገረበትን ሁኔታዎች ሁሉ ስንመለከት በመታዘዛቸው ላይ የተመሰረተ አልነበረም፤ ሆኖም ወደፊት ሊያደርግ ላለው ነገር ግን ቅድመ ሁኔታ አድርጎ የሚናገረው ነገር የእነርሱን መታዘዝ የሚጠይቅ ነው። እግዚአብሄር የሚላቸውን ከታዘዙና ቃል ኪዳኑን ከጠበቁ 1ኛ. ለእግዚአብሄር ርስት ይሆናሉ፣ 2ኛ. የመንግሥቱ ካህናት ይሆናሉ፣ 3ኛ. ለእግዚአብሄር የተቀደሰ ህዝብ ይሆናሉ።
5. በዚህ ክፍል ውስጥ ሙሴ በሁለቱ ማለትም በእግዚአብሄርና በህዝቡ መሃል ሆኖ ቁ7 የእግዚአብሄርን ለሕዝቡ፣ ቁ8 ደግሞ የህዝቡን ለእግዚአብሄር የሚያስተላልፍ ማዕከለኛ ሰው ሆኖ መቅረቡ ካህን ሊያሰኝ የሚያስችለውን ነገር አድርጓል ማለት እንችላለን። ወደ እግዚአብሄር መቅረብ ዛሬም ውጫዊ ባይሆንም የልብ ዝግጅት ይጠይቃል እላለሁ፤ ለዚህም ያዕ 4፡8-10 ብናነብ አጠር ባለ መልኩ ወደ እርሱ ለመቅረብ የሚጠይቀውን ነገር ያዕቆብ አስፍሮልናል።
6. ወደ እግዚአብሄር ተራራ መቅረብን አስመልክቶ በቁ12-25 ባሉት ክፍሎች ተከፍለው የሚታዩት፤ ሙሴ ለብቻው፣ አሮን ለብቻው፣ ካህናቱ በአንድ መደብና፣ በመጨረሻ ደረጃ ደግሞ ሕዝቡን በሌላ መደብ ለይቶ ማየት ይቻላል። ይህንን ዘመን አስመልክቶ አማኞች አንደኛው ከሌላው መበላለጥ ሳይኖር ሁላችንም ወደ እግዚአብሄር ዙፋን በድፍረት መግባት እንደተሰጠን በኤፌ 2፡18፣ ዕብ 4፡16 እና ከመሳሰሉት ክፍሎች መረዳት እንችላለን።
7. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናየው ነገር ለማንኛውም ሰው እንኳንስ ወደ ተራራው ለመቅረብና ለመንካት ቀርቶ ከሩቅ ለማየት እንኳን ለማየት እንኳን የሚያስፈራ፣ ሁኔታው ሁሉ በአብዛኛው በእግዚአብሄር ቅድስና ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ በያዕቆብ ውስጥ የምናነበው ደግሞ ወደ እግዚአብሄር የመቅረብና የመጢጋት ጥሪ መደረጉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው የጸጋ ብዛት ምን ያህል ትልቅ እንደሆነና ሊያስገርመን፣ ሁልጊዜ ልንደነቅበትና ልናመሰግንበት የሚገባን እውነት እንደሆነ ነው የተረዳሁት።

<u>ጥናት አስራ ስምንት ዘፀአት 20፡1-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. እነዚህን አሥር ትዕዛዛት ሌሎች መከፈል የሚቻሉባቸው ሌሎች መንገዶች ሊኖሩ ቢችሉም እንኳን፤ ለብዙዎች ሰዎች ግን ግልጽ ሆኖ ሊታይ እንደሚችል የማምነው አንድ መንገድ ግን፤ ከእግዚአብሄር ጋራ ባለ ግንኙነት ላይ ያተኮሩና፣ ሌሎቹ ደግሞ ከጎረቤት ወይም ከሰው ልጆች ጋራ በሚደረግ ግንኙነት ላይ ያተኮሩ እንደሆኑ ማየት ይቻላል።
2. የመጀመሪያዎቹና እግዚአብሄር እንደሚቀጣቸው የተናገራቸው ሰዎች በቁ5 ላይ የምናያቸው እርሱን የሚጠሉትን ሲሆን፤ ሁለተኛዎቹ ሰዎች ደግሞ በቁ6 ላይ የምንመለከታቸው እግዚአብሄርን የሚወዱና ትዕዛዛቱን የሚጠብቁት ሰዎች እንደሆኑ ነው የሚነግረን። በቁ5 ላይ ቁጣውን አስመልክቶ ሲናገር እስከ ሶስትና አራት ትውልድ ድረስ ሲል፤ በቁ6 ውስጥ ደግሞ ፍቅሩን ለምን ያህል ጊዜ እንደሚጠብቅ ሲነግረን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ በማለት ፍቅሩ ከቁጣው በብዙ እጥፍ እንደሚበልጥ ያመለክተናል።
3. ይህንን ትዕዛዝ በተለያዩ መንገዶች መስበር እንደሚቻል ቢታወቅም፤ እነዚህ ጥቅሶች የሚያሳዩኝ ነገር ቢኖር ሰዎች ራሳቸው በአንደበታቸው የእግዚአብሄርን ስም እየጠሩ ከመሳደብ ውጭ በየእለት ኑሯችን የእግዚአብሄርን ስም በማሰደብ ወይም ደግሞ በማስከበር ለትዕዛዙ ያለንን ሁኔታ መግለጽ እንችላለን።
4. በዘጸ 20፡8 ላይ ለእስራኤል ህዝብ የተሰጠው የሰንበት ትዕዛዝ እኛ አንድ ቀን ለይተን ሥራ አለመሥራት በሚል አልወስደውም፤ ምክንያቱም የቆላስይስንና የእብራዊያንን ጥቅሶች ስንመለከት በተለይም ቆላስይስ እንደሚነግረን ሰንበት ሊመጣ ላለው ነገር ጥላ እንደሆነና ያ ሰንበት ጥላ የሆነለት ነገር ስለመጣ በጥላው ሥር መመላለስ አይኖርብንም። አማኝ ሰንበትን ማክበር አለበት ብዬ እላለሁ፤ ይህም ማለት ሰንበት ከሥራ ማረፍ ማለት ስለሆነ ክርስቶስ ስራችንን ሰርቶ ስለጨረሰልን እያንዳንዱን ቀን ሥራ ሰርቼ የማገኘው ነገር እንደሌለ በመገንዘብ ክርስቶስ በሰራው ሥራ ላይ ማረፋችን ሰንበትን አከበርነው ብዬ እላለሁ።
5. ጳውሎስ በኤፌሶን 6፡2-3 ውስጥ ከሰነዘራቸው ሃሳቦች መሃል ይኸንን ከአስርቱ ትዕዛዛት ውስጥ አምስተኛውን ልዩ እንደሆነ የተናገረው፤ ይህ ትዕዛዝ ብቻ ከተስፋ ቃል ጋራ የተያያዘ እንደሆነ በመናገር ልዩነቱን አሳይቶናል። በአለም ላይ ያሉ አማኞችም ሆኑ የማያምኑ ሰዎች አብዛኛው ሰው ገድሎ የማያውቅ ነው፤ ሆኖም እንደ ዮሐንስ አነጋገር ከሆነ ሌላን ሰው መጥላት ሰው መግደል ስለሆነ አብዛኛዎቻችን ነፍሰ ገዳይነትን ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንደተለማመድነው እገምታለሁ።
6. ሙሴ የህዝቡን ፍርሃትና ድንጋጤ ካረጋጋ በኋላ ለምን እግዚአብሄር በዚህ ዓይነት አስፈሪ መንገድ መናገር እንዳስፈለገው ሲናገር፤ እግዚአብሄር ይህንን ያደረገው ወደፊት እናንተ ሃጥያትን እንዳትሰሩ ያያችሁት የሚያስፈራ ሁኔታ እንዲከለክላችሁ እንጂ ሊገላችሁ አይደለም። እግዚአብሄር ሁልጊዜ አላማው ሕዝቡን ማስፈራራት ሳይሆን በማንኛውም መንገድ እርሱን መፍራትና ከሃጥያት መራቅ እንዲለማመድ ማድረግ ነው።
7. በዘጸ 20፡23 ላይ እንደገና በድጋሚ ሲነገሩ የምናገኛቸው ትዕዛዛት በቁ3 እና በቁ4 ላይ ሰፍረው የሚገኙት አንደኛውና ሁለተኛው ትዕዛዛት ናቸው።
8. እግዚአብሄር እነርሱን ከፈርዖን የባርነት ቀንበር ነጻ እንዳወጣቸው ሁሉ፤ እኛንም አስከፊ ከሆነው ከሃጥያት ባርነት በክርስቶስ ሞት ነጻ አውጥቶናል። እስራኤላውያንን በቃ ከግብጽ ባርነት ነጻ ወጥታችኋልና ከአሁን በኋላ እንደፈለጋችሁት መኖር ትችላላችሁ እንዳላለና ለእርሱ ብቻ እንዲገዙ፣ እርሱን እንዲያገለግሉና ለእርሱ ብቻ እንዲኖሩ ትዕዛዛትን እንደሰጣቸው ሁሉ፤ እኛንም ከሃጥያት ባርነት ነጻ ያወጣን ከአሁን በኋላ የጽድቅ ባሪያዎች በመሆን ለቃሉ በመታዘዝ እንድንኖር ነው።

# ጥናት አስራ ዘጠኝ ዘፀአት 23፡1-33 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሀ) የሃሰት ወሬ አለመንዛት ለ) ተንኮል ያለበት ምስክርነት በመስጠት ክፉን ሰው ማገዝ እንደማይገባ ሐ) ክፉ በማድረግ ብዙዎችን አለመከተል መ) በምስክርነት ጊዜ ብዙዎችን ተከትሎ ፍርድን አለማጣመምና ሠ) በዳኝነት ጊዜ ለድሃ አለማድላት የሚሉ ናቸው። ከእነዚህ አምስቱ መሃል በእኔ አመለካከት በአንደኛ ደረጃ ለአማኞች ፈተና ሆኖ ሊገኝ ይችላል የምለው ነገር የመጨረሻው ማለትም "በዳኝነት ጊዜ ለድሃው አታድላ" የሚለው ይመስለኛል፤ ምክንያቱም አማኙ እግዚአብሄር በድሆች ላይ ፍርድ ሲጣመም እንደማይወድ ስለሚያውቅ ሁልጊዜ ተበዳይ ድሃው እንደሚሆን ስለምንገምት ይመስለኛል።
2. እንደ እኔ አስተሳሰብ ከሆነ በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ላይ ሰፍረው የማያቸው ሁለቱ ትዕዛዛት ከአዲስ ኪዳን ትምህርት ጋራ በደንብ የሚስማሙ ሆነው ነው የማያቸው፤ ይህንንም ሃሳብ ይደግፋል ብዬ የማምነው ጥቅስ በማ5፡43፣ በሮሜ 12፡20 እና ከመሳሰሉት ጋራ ማነጻጸር ይቻላል እላለሁ። በቁ6 ላይ እንደተነገረውና እግዚአብሄር ለድሃው ፍርድ እንዳይጓደልበት የሚፈልገውን ያህል በቁ3 ላይ ደግሞ ሰውየው ደሃ ስለሆነ ብቻ በፍርድ ጊዜ ለእርሱ ማድላትንም የማይወደው ነገር እንደሆነ በመንገር ሚዛናዊነቱን ማየት ይቻላል።
3. የመጀመሪያው ነገር፤ ጉቦን መቀበል አጥርተው የሚያዩትን ሰዎች ዓይን እንደሚያሳውርና የጻድቃንንም ቃል እንደሚያጣምም ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ፤ መጻተኛውን እንዳይጨቁኑ በግብጽ በነበሩበት ጊዜ የሆነባቸውን ነገር ቢያስታውሱ ስሜቱ ሊገባቸው እንደሚችል ነው የሚነግራቸው። አጥርቶ የሚያይን ሰው ማሳወር፣ ጻድቅ የሆነውን ሰው ቃልም ማጣመም የሚችል ከሆነ በ1ኛ ቆሮ 10፡12 ላይ የሚቆም የሚመስለው እንዳይወድቅ እንዲጠነቀቅ የሚናገረውን የሃዋርያውን የጳውሎስ ምክር ሥራ ላይ ማዋሉ ብልህነት ነው። እግዚአብሄር አምላክ ጉቦን ላለመቀበል እንደምሳሌ አድርጎ የሚያቀርብልን ራሱን ነው።
4. ጉቦ የጻድቁን ቃል ሊያጣምም እንደሚችልና አጥርቶ ማየት የሚቻለውን ብልህ ሰው እንኳን ሊያሸንፍ እንደሚችል ካመንን፤ በአገራችን የሚገኙትም ቅዱሳን በተለይም ኑሮን ማሸነፍ የሚቸገሩ ብዙዎች ስላሉ ይህ ሁኔታ አስቸጋሪ የሆነ እርምጃ ማለትም በረሃብ እሞታለሁ እንጂ አምላኬን አላሳዝንም ወደሚለው ውሳኔ ላይ መምጣት ግድ ይሆንባቸዋል ማለት ነው። መጽሐፉ ብዙ ትኩረቱን ያደረገው በጉቦ ተቀባዮች ላይ ነው፤ ጉቦን መስጠት ሃጥያት እንደሆነ የሚናገር ክፍል ፈልጌ ለራሴ ማግኘት አልቻልኩም፤ ሆኖም በቀጥታ የሚከለክልም ባይሆን ጳውሎስ ተጠይቆ እንዳላደረገው የሚናገር ክፍል ከሐዋ 24፡26ን ብቻ አግኝቻለሁ።
5. ምድሪቱን ስድስት ዓመታት አርሶ በሰባተኛው ዓመት የማሳረፉ ምክንያት ድሆች ምግብ እንዲያገኙና የዱር አራዊቶችም የሚመገቡት ነገር እንዲኖራቸው ሲሆን፤ ስድስት ቀን ሰርቶ ሰባተኛውን ቀን ማረፍ ደግሞ ከበሬና ከአህያ ጀምሮ፣ በቤቱ ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ እረፍት ስለሚያስፈልገው ነው። ለእነዚህ ትዕዛዛት ከተሰጡት ምክንያቶች የምማረው ነገር ቢኖር እግዚአብሄር ምን ያህል ለድሆችና ለመጻተኞች እንዲሁም ለእንሣትም ጭምር እንደሚገደው ግልጽ ሆኖ አየዋለሁ።
6. ሶስቱ መከበር ያለባቸው በዓላት፤ ያልቦካ የቂጣ በዓል፣ የመከር በዓልና፣ የመከተቻ ወይም የመሰብሰቢያ በዓል የሚሉት ናቸው። እግዚአብሄር የሚናገራቸውን ነገሮች በደንብ አድርገው በጥንቃቄ ሲያደምጡና፤ ከማድመጥም ደግሞ አልፈው የተባሉትን ሁሉ ሲያደርጉ ያን ጊዜ እርሱ ለጠላቶቻቸው ጠላት፣ የሚቃወሟቸውንም ደግሞ እንደሚቃወም እርግጠኞች መሆን ይችላሉ።
7. በነዚያ ቁጥሮች ውስጥ ብዙ የተስፋ ቃሎች ቢኖሩም፤ በመሃል ላይ ቁ24ን ስናነብ ለአህዛብ አማልክት እንዳይሰግድ፣ እንዳያመልካቸው፣ ልምዳቸውን እንዳይከተልና፣ ከዚያም ባሻገር እንዲያፈራርሳቸውና ድንጋዮቻቸውን ሁሉ እንዲሰባብር ከእስራኤል ይጠበቃል።
8. ምንም እንኳን ጠላት ወዲያው በቅጽበት ቢጠፋና ያለ ጦርነት በሰላም ተዝናንቶ የመኖር ፍላጎት የማንኛውም የሰው ልጅ ፍላጎት እንደሆነ ይታወድቃል፤ እግዚአብሄር ግን ጠላቶቻችሁን አጠፋላችኋለሁ የሚል እርግጠኛ የሆነ ቃል ቢገባላቸውም እንኳን ወዲያው ግን እንደማያደርገው ግልጽ አድርጎ ነግሯቸዋል፤ ምክንያት አድርጎ ያቀረበውም ሁሉም በአንዴ ማጥፋት ለዱር አራዊት መራባት ሁኔታውን ስለሚያመቻችላቸው ቀስ በቀስ መሆኑ ለራሳቸው ደህንነት መሆኑን ነው የነገራቸው።

# ጥናት ሃያ ዘፀአት 32:1-35 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንደ አንደኛ ምክንያት ሆኖ የማየው የትዕግሥታቸውን ማለቅ ወይም ደግሞ ለመጠበቅ አለመቻላቸውን መግለጻቸው ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ እስከዛሬ ድረስ እግዚአብሄር በመሃላቸው የሚሆንና የሚታይ ወኪል እንደነበረው፤ ዛሬ ግን ያ ወኪል የነበረው ሙሴ ከአይናቸው ሲጠፋ የሚያዩት ነገር መፈለጋቸውን ስውር ምክንያት አድርገን ማየት እንችላለን። አሮን ሃላፊነቱን በሚገባ አልተወጣም የሚያሰኘኝ የመጀመሪያው ነገር "አይሆንም" ማለት አይችልም፤ "ከግብጽ ያወጣን ሙሴ" ብለው ሲናገሩ ከግብጽ ያወጣቸው እግዚአብሄር እንጂ ሙሴ እንዳይደለ አለመናገሩና፤ ሃላፊነቱን አብሮ የተቀበለውን ሖርን አለማማከሩ የአመራሩን ድካም ይጠቁመኛል።
2. የሰው ልጅ ሲባል እንኳን ወርቅ ይቅርና የራሱ የሆነውን ትንሽ ነገር እንኳን በቀላሉ አይሰጥም፤ በዚህ ክፍል እስራኤላውያኑ ወርቃቸውን አውልቀው እንዲሰጡ ሲጠየቁ ወዲያው ያለክርክር መስጠታቸው ምን ያህል ልባቸው የሚታይ አምላክ ይጠማ እንደነበረ ነው የሚያሳየኝ። እስራኤላውያኑ ይህንን በማድረጋቸው ከአስርቱ ትዕዛዛት መሃል "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ" እና "በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ" የሚሉትን የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ትዕዛዛት ነው የጣሱት።
3. የዚህ ህዝብ እውነተኛው ባለቤትና ከግብጽ ምድር ባርነትም ነጻ ያወጣው እግዚአብሄር ለመሆኑ የሚያጠራጥር ነገር የለም፤ ሆኖም በዚህ ሥፍራ እግዚአብሄር ሕዝቡን የሙሴ ሕዝብና፣ ሙሴ ከግብጽ እንዳወጣው መናገሩ በሕዝቡ መከፋቱን የሚያሳይበትና ሕዝቡም ራሳቸው በቁ1 ላይ ከግብጽ ያወጣቸው ሙሴ እንደሆነ የሚናገሩትን ለማንጸባረቅ ይመስለኛል።
4. በሰፈሩ ውስጥ ይሰማ የነበረው ድምጽ ለኢያሱ የጦርነት ድምጽ እንደሆነ ሲሰማው፤ ለሙሴ ግን ድምጹ የድልም ድምጽ ወይም ደግሞ የሽንፈትም ድምጽ እንዳልሆነ ነገር ግን የዘፈን ድምጽ መሆኑን ነው የገለጸው። ይህንን በህዝቡ ዘንድ ይሰማ የነበረውን ድምጽ ምንነት ለይቶ ለማወቅ ሙሴ ከኢያሱ ይልቅ የተሻለ እድል ነበረው ማለት የሚያስችለኝ ነገር ቢኖር፤ በቁ7 ላይ ሙሴ ህዝቡ እየዘፈኑ ነው ተብሎ በቅጥታ ባይናገረውም እንኳን በህዝቡ ዘንድ እየሆነ ያለውን ነገር በቀጥታ ከእግዚአብሄር ከራሱ አፍ የሰማ ስለሆነ ጦርነት እንዳልነበረ ማወቅ ችሏል ብዬ አምናለሁ።
5. ሙሴ በሁኔታው እጅግ በተናደደበት ጊዜ አንዱ ያደረገው ነገር በእጁ የነበሩትን ጽላቶች መስበር ነው። ሁለተኛ ያደረገው ደግሞ የሰሩትን ጥጃ ወስዶ በእሳት ማቃጠል፤ ዱቄት እስኪሆን ድረስ ፈጭቶ ውሃ ውስጥ መበተን፤ እንዲሆም ውሃውን እስራኤላውያኑ እንዲጠጡት ማድረግ ነው። በቁ21 ላይ እንደምንመለከተው ለዚህ ድርጊት የመጀመሪያ ተጠያቂ ያደረገው ሰው ቢኖር ሕዝቡን እንዲመራና እንዲጠብቅ ሃላፊነት ሰጥቶት የሄደውን አሮንን ነው።
6. ሙሴ ባጉረመረሙና እርሱ በሃይሉ ማድረግ የማይችለውን ነገር በጠየቁትና በተቆጡ ጊዜ የወሰደው እርምጃ ወደ እግዚአብሄር መጮህ ሲሆን፤ አሮን ግን ስጠኝ የተባለውን ነገር ሕዝቡን በመፍራት እንደሰጣቸው እናያለን። ከዚህ የምንማረው አንድ መሪ በሕዝብ ስለተጠየቀ ብቻ የተባለውን ከማድረጉ በፊት ከእግዚአብሄር ጋራ የመማከር ልምድ ማዳበሩ አስፈላጊ እንደሆነ እንማራለን።
7. በማቴ 10:37 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ ደቀመዝሙር መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆን የገለጸበት መንገድ ቤተሰብን እንኳን መጥላት ቢያስፈልግ እዚያ ደረጃ መሄድ እንደሚጠይቅ ሲሆን፤ በዚህ በዘጸዐቱ ክፍል ደግሞ የምናየው ከእግዚአብሄር ጋራ መወገን ካስፈለገ ቤተሰብን ከመግደል መመለስ እንደሌለ ያሳየናል። ሙሴ ከህዝቡ ጋራ ሲሆን ለሃጥያት የሚለሳለስ፣ ግድ የለም ምንም አይሆንም የሚል ዓይነት መሪ እንዳልሆነና እንዲያውም ጨካኝ የሚመስል መሪ ሲሆን፤ በእግዚአብሄር ፊት ሲመጣ ግን ሙሴ ለሚመራው ሕዝብ ምን ያህል የሚገደው፣ የሚቆረቆርና ራሱን እንኳን አሳልፎ ለመስጠት ወደኋላ የማይል መሪ እንደሆን እንረዳለን።
8. ሙሴ እግዚአብሄርን ለመማጸን ሲቀርብ ተጠቀመበት ብለን ከክፍሉ ውስጥ ሌላ ሃሳቦችን መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም እንኳን፤ አንዱ በዋነኛነት ሊታይ የሚገባው ነገር እግዚአብሄር አምላክ አስቀድሞ ለባሪያው ለአብርሃም፣ ከዚያም በመቀጠል ለልጁ ለይስሃቅና ለልጅ ልጁ ለያዕቆብ የገባውን የተስፋ ቃል በማሳሰብ ነው ልመናውን የዘጋው።

<u>ጥናት ሃያ አንድ ዘፀአት 33፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ሙሴ እግዚአብሄርን ለመገናኘት በሄደበት ወቅት ሕዝቡ በፈጸሙት ሐጥያት እግዚአብሄር እጅግ ያዘነና የተቆጣ መሆኑን ነው የምንመለከተው፤ ከህዝቡ ጋራ ማደርና መሆን የሚፈልገው አምላክ ዛሬ ከህዝቡ ጋራ መሆን እንደማይፈልግ ግልጽ አድርጎ ነው ለባሪያው ለሙሴ የተናገረው። በእግዚአብሄር ውሳኔ የተሰማቸው ሶስቱ መገለጫዎች፡ ሀ) አባባሉ እንዳሳዘናቸው ለ) አባባሉ ትካዜ ውስጥ እንዳስገባቸውና ሐ) ሕዝቡ ሁሉ ጌጥ የሚባል ነገር ላለማድረግ ወሰኑ።
2. እግዚአብሄር ለአባቶቻቸው የገባውን ቃል ኪዳን በመፈጸም ወደ ተስፋይቱ ሃገር እንደሚያስገባቸው፣ እንዲሁም በአካባቢው የሚገኙትን የተለያዩ መንግሥታት እንደሚያስወጣላቸው የተናገረ ቢሆንም እንኳን፤ የሕዝቡን ልብ ያሳዘነው አንድ ነገር ቢኖር እግዚአብሄር ራሱ ከእነርሱ ጋራ ሳይወጣ በመልዓኩ በኩል የሚፈጸም ነገር መሆኑ ነው ያሳዘናቸው።
3. በዘጸ 32፡2 ውስጥ ጌጦቻቸውን አውልቀው ለአሮን እንዲሰጡት የተጠየቁበት ምክንያት፤ በፊት ለፊታቸው ሊያዩና ሊያመልኩት የሚችሉት ጣዖት እንዲሰራላቸው በማሰብ ሲሆን፤ በዘጸ 33፡5-6 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ጌጦቻቸውን እንዲያወልቁ የተጠየቁት ከእግዚአብሄር ጋራ የተበላሸው ግንኙነታቸው እንዲታደስ፤ ምናልባትም ደግሞ ቆይተው ቀድሞ ያደረጉት ዓይነት ድርጊት ውስጥ ተመልሰው ለመግባት የመሳት ምክንያት እንዳይሆናቸው ይሆናል ብዬ አስባለሁ።
4. ሕዝቡ እግዚአብሄርን ለመጠየቅ ወይም ከአምላኩ ጋራ ለመገናኘት እንዲችል የተዘጋጀለት ሥፍራ ከሚኖሩበት ሰፈር ወጣ ብሎ የተተከለ የመገናኛ ድንኳን በመባል የሚጠራ እንደነበረ ነው የምናነበው። በዚህ ክፍል ውስጥ ሕዝቡ ከአምላካቸው ጋራ ለመነጋገር ወይም ለመጠየቅ ከሰፈራቸው መውጣት እንደነበረባቸው ሁሉ፤ እኛም ዛሬ ከእግዚአብሄር ጋራ ጥራት ያለው ጊዜ ለማሳለፍ ከተፈለገ ውክቢያና ግርግር ከበዛበት ሁኔታ ውስጥ ራሳችንን አግልለን በተቻለ መጠን በአካል ርቀን መውጣት እንኳን ባያስፈልገን ከሁኔታዎች ራሳችንን ወጣ ማድረግ እንደሚኖርብን ነው የሚያሳየኝ።
5. ሙሴ እግዚአብሄር አምላክ እርሱን በስሙ እንዳወቀው የተነገረውን እውነት እንደተቀበለ፤ ሆኖም ከዚያ ባሻገር ሙሴ የሚጠማው ነገር እንደነበረ፤ ስለዚህም "አንተን አውቅህና፤ ያለማቋረጥ በፊትህ ሞገስ አገኝ ዘንድ መንገድህን አስተምረኝ" በማለት እግዚአብሄር ሙሴን እንዳወቀው፤ ሙሴም እግዚአብሄርን ማወቅ እንደሚፈልግ ያረጋግጥለታል። ለእኔ እንደሚገባኝ ከሆነ እግዚአብሄርን ማወቅ መቼም ቢሆን አውቄ ጨርሼዋለሁ የምንለው ነገር ስላልሆነ፤ እንዲያውም ባወቅነው ቁጥር ገና እንዳላወቅነው የሚያረጋግጥልን ስለሆነ ሙሴም ይህንን በጥልቅ ስለተረዳ ይመስለኛል እግዚአብሄርን ማወቁን የሁልጊዜ ጥያቄው አድርጎ የያዘው።
6. በቁ15 እና በቁ16 ላይ ሙሴ የእግዚአብሄርን ሕዝብ ከሌሎቹ በገጸ ምድር ከሚገኙት ሕዝቦች ጋራ የሚለይ ትልቅ ነገር እንዳለ ሲናገር፤ ይህ እስራኤልን ከሌሎቹ ሕዝቦች የሚለየው ዋነኛ ነገር የእግዚአብሄር አምላክ ከህዝቡ ጋራ መገኘትና በመሃላቸው ማደሩ እንደሆነ ይነግረናል።
7. በቁ15 ላይ ከምናነበው ከሙሴ አነጋገር ለህይወታችን መማር የምንችለው ትልቅ ነገር እንደሆነ የማምነው፤ ያለ እግዚአብሄር ማርና ወተት በምታፈሰው በከነዓን፤ ማለትም ምቹና ሁሉ ነገር የተሟላ በሆነበት ሥፍራ ከመኖር ይልቅ፤ ሁኔታዎች ምቹ ባልሆኑበት፣ ውሃና ምግብ እንደልብ ሊገኝ በማይችልበት የከባድ ሕይወት ምሳሌ በሆነው በምድረበዳ ከእግዚአብሄር ጋራ መኖር እጅግ ሊመረጥ የሚገባው ነገር እንደሆነ ነው ከሙሴ አነጋገር መረዳትና መማር የምንችለው።